# ፍቅርና ሰላም

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚታተም ወርሃዊ ጋዜጣ

A Monthly Amharic/English Newspaper Published by the Catholic Bishop's Conference of Ethiopa (CBCE)

General Secretariat/ECS

# LINK

ካቶሊካዊ ሲኖዶስ 2014 2016

ለሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያን

ኅብረት / ተሳትፎ / ተልእኮ

ቁጥር 570 | ጥቅምት 2017 ዓ.ም | ዋጋው የኢት. 15.00 ብር


# 16ኛው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የብፁዓን ጳጳሳት ሲኖዶስ በቅድስት መንበር ተካሄደ

### የእያንዳንዱን ካቶሊካዊ እምነት ጉዞ ለመዳሰስ ያለመ ሦስት ዓመት



ርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቺስኮስ፥ ከመስከረም 22 እስከ ጥቅምት 17 ቀን 2017 ዓ. ም. የተካሄደውን የቅዱስ ሲኖዶስ መደበኛ ጉባኤ ሁለተኛ ምዕራፍ በቅዱስ ጴጥሮስ አደባባይ ባሳረጉት የመስዋዕተ ቅዳሴ ጸሎት በይፋ አስጀምረዋል።

ወደ ገፅ 3 ዞሯል



## ብፁዕ ወቅዱስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ መልዕክት ለወጣቶች

ወደ ገፅ 4 ዞሯል



## ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ ክቡር አባ ተስፋዬ ታደሰን የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ረዳት ጳጳስ ብለው መሰየማቸውን ቫቲካን ጥቅምት 27 ቀን 2017 ዓ.ም. አወጀ

ወደ ገፅ 3 ዞሯል



## ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ ክቡር አባ ኀበዘአየሁ ጌታቸውን የሀዋሳ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ብለው መሰየማቸውን ቫቲካን ህዳር 6 ቀን 2017 ዓ.ም. አወጀ

ወደ ገፅ 3 ዞሯል

## 50ኛው የወርቅ ኢዮቤልዩ ዓመት

መስከረም 1967 ዓ.ም. የመጀመሪያው እትም ታተመ። በዚያን ጊዜ ጋዜጣውን ያስጀመሩት አባቶች መልዕክት እነሆ

ወደ ገፅ 7 ዞሯል

የብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ የ25ተኛ የጵጵስና የብሩራዊ ኢዮቤልዩ ዓመትን በማስመልከት ሥጦታ ለማቅረብ ለሚፈልጉ ሁሉ የቁሳዊ ሥጦታ ቀርቶ የትምህርት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወጣቶች እንደሚውል በማሰብ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ የሚል የገንዘብ ድጋፍ ዕድል መመቻቸቱን ገልጸው በተዘጋጀው የባንክ አካውንት መላው ካቶሊካውያን እና በጎ ፍቃድ ያላቸው ሁሉ ለዚህ በጎ አድራጎት ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

**Cardinal Berhaneyesus Fund**

Account Name: **Cardinal Berhaneyesus Fund**

Account Number: **1000523294338**

Commercial Bank of Ethiopia, Mahatema Gandhi Branch

Swift Code: **CBETETAA**

# ፍቅርና ሰላም

መስከረም 1967 ዓ. ም. ተጀመረ

አሳታሚ ቤተ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የማኅበራዊ መገናኛና ሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ በየወሩ ተዘጋጅቶ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዋና አዘጋጅ | አባ አበራ ማኬቦ | ፕሩፍ ሪደር | የምሥራች አሰፋ |
| ምክትል ዋና አዘጋጅ | አቤል ሙሴ | ሌይ አውት 1 | ጨረቃ ዘውዴ |
| ማኔጂንግ ኤዲተር | ቤዛዊት አሰፋ | ሌይ አውት 2 | ቤተልሔም ታደሰ |
| ተቀዳሚ ረዳት አዘጋጅና ሪፖርተር/ኤዲተር | ገብሩ ሃ/ዮሐንስ | ስርጭት | ማኅበራዊ መገናኛና ሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ |
| ምክትል ረዳት አዘጋጅ | መሳይ ማሪዮ | | |


ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ ስልክ - (0111) 55 03 00 ፋክስ (0111) 55 31 13 E-Mail - scpr@eccsdco.org Website - https//www.cbce-gs.org

# ርዕሰ አንቀጽ

# የሲኖዶሱ ውሳኔዎች የእኛም ውሳኔ




የቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓተ አምልኮ መሰረቱ "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃአችሁ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (ማቴ. 28፡-19)። በዚህ ቃል ኪዳን መሰረት ቤተክርስቲያን ግልጽ ተልዕኮ አላት። በዘመናችን ሲኖዶሳዊነትን መኖር ማለት የሁለተኛውን የቫቲካን ጉባዔ ሙሉ ትግበራ አንድ እርምጃ መውሰድ ማለት መሆኑን አንዘንጋ። ይህም ማለት ከመነሻው ቤተ ክርስቲያን መሆን ለሁሉም ሰው የሚሆን ቦታ ያለው እና ሁሉም ሰው ዋጋ ያለው ማህበረሰብ፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር የሚለማመዱ እና መግባባት የሚፈልጉ ኃጢአተኞች ይቅር የተባሉ ማኅበረሰቦች የሚኖሩባት፣ ለሁሉም ክፍት የሆነች ቤተክርስቲያን መሆን መቻል ማለት ነው።

ከዛሬ 62 ዓመት በፊት በሮም ቫቲካን የተደረገው 2ኛ የቫቲካን ጉባኤ ከመላው ዓለም የተሰባሰቡት አባቶች በዘመናዊ ዓለም የቤተክርስቲያናችንን ጉዞ በተመለከተ ወቅቱን በማገናዘብ መሰረታዊ የእምነት ቀኖና መርህ ሳይዛነፍ መጓዝ ግድ መሆኑን የመሰከረችበት ዘመን ነበር። በዚህ እርሾ መነሻነት ከዚያ ጊዜ አንስቶ የጊዜውን ምልክት በመዋጀት በተለያየ ርዕስ ላይ ሲኖዶሳዊ ጉባኤዎች አድርጋለች። በቅርቡ ከመስከረም 22 እስከ ጥቅምት 17/2017 ዓ. ም. ሲኖዶሳዊ ጠቅላላ ጉባኤ በሮም ቅድስት መንበር የተደረገው በ2015 ዓ.ም ቀጣይ ነበር። በዚህ ሁለተኛ ዙር የሲኖዶስ ጉባኤ 351 ተሳታፊዎች ሲገኙ 272 ብፁዓን ጳጳሳት ሲሆኑ 96 ጳጳሳት ያልሆኑትና ጥሪ የተደረገላቸው የሃይማኖት አባቶች ከመላው ዓለም በአንድ ሃሳብ ፣በአንድ ልብ፣ የመከሩበት ጉባኤ ነበር።

የሲኖዶሱ ጉባኤው በዋናነት ጳጳስ ከፍተኛ ቁጥር የያዙት ጳጳሳት የጥምቀት ምስጢርን ለተቀበሉት ምዕመናን ከመንፈስ ቅዱስ እንደተሰጣቸው በማሳወቅ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ድምፅ ለመላው ሕዝብ በማሰማት እና እምነት እንዳይሳሳት በማድረግ ግንባር ቀደም ደቀ መዝሙር በመሆናቸው ነው።

የሲኖዶስ ጠቅላይ ጸሐፊ ብፁዕ ካርዲናል ማርዮ ግሬች በንግግራቸው ፥ "ዛሬ የሚጀምረው የሲኖዶስ ጉባኤ የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የሰውን ልጆች ሕይወት በማዳበር እና በመንፈስ ቅዱስ በማደስ ሲኖዶሳዊ እና ሚሲዮናዊ ቤተ ክርስቲያን እንድንሆን ያስችለናል" ብለዋል ።

በመቀጠልም "የሲኖዶሱ ተሳታፊዎች ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የመጡ፣ ሁሉም የየራሳቸው መንፈሳዊ ሃብት፣ የራሳቸው ተግዳሮቶች፣ ራሳቸውን ማደስ የሚፈልጉ እና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለዛሬው ዓለም ለመመስከር አዲስ መንገድ እና አዲስ ቋንቋ ለመፈለግ ቢመጡም፥ በእነዚህ ቀናት ውስጥ የቤተ ክርስቲያኗን መንፈሳዊ እሴቶች ባልተከፋፈለ እና ማንንም ወደ ጎን በማያደርግ የጋራ መንፈስ ለመጋራት ተቀምጠናል" ብለዋል።

በተለይም "የቤተ ክርስቲያን አስተምህሮን በተሳሳተ መንገድ በመጠቀም በሰላም፣ በስነ ፍጥረት ፣ በአገሬው ነባር ተወላጆች፣ በስደተኞች፣ በሴቶች፣ በቤተሰብ፣ በወጣቶች ላይ የሚፈጸሙ ያልተገባና ፀያፍ ድርጊቶች በድህነት እና በሲኖዶሳዊነት ላይ የተሠሩ ክፉ ድርጊቶች ለማሸነፍ ተጠናክረን የምንወጣበት ጉባኤ ነው" ብለዋል።

በጉባኤው ላይ ከ40 በላይ ጥናታዊ ጽሁፎች ለውይይት የቀረቡ ሲሆን ከብዙ ጥቂቱ የሚከተሉትን ያካተተ ነበር።

- የእግዚአብሔር ሕዝብ የተልዕኮ ግብ
- በአጥቢያ እና በኩላዊት ቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው የጋራ ግንኙነት
- በሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጳጳስ ሚና እና ሥልጣን
- የርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ተግባር እና የብፁዓን ጳጳሳት ሲኖዶስ ተልዕኮ
- ምእመናን እና በተለይ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸው ሚና፣
- በድህነት እና በስቃይ ውስጥ ያሉትን እና ከማህበረሰብ እና ከቤተ ክርስቲያን እንደተገለሉ የሚሰማቸውን የተፋቱትን፣ የተገለሉትን ቀርቦ ከልብ ማዳመጥ እና መፍቴ የመስጠት ሃላፊነት፡-
- ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ ባህሎች እና ሃይማኖቶች ፍልስፍናዎች ጋር ተጨማሪ ውይይት እንዲደረግ መጣር፤ መልካም ግንኙነት መፍጠርና እና ራሷም ድልድይ መሆን መቀጠል እንዳለባት፡-
- ለአዳጊ ልጆች የሚስጥ መሠረታዊ ክርስትና እምነት ትምህርት ማሳደግ፡-
- ምእመናን ፣ ከጳጳሳት እና ከካህናት ጋር ያላቸው ትብብር እና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ያላቸው ተሳትፎ ሚና
- የማህበራዊ ሚዲያ ሚና ለበጎነት መጠቀም በተለይ አዲሱን ትውልድ ከዲጂታል ሐዋርያዊ አገልግሎት ጋር እንዲጠቀም መጣር፡-
- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እና እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን እና በዓለም መካከል ላሉት ግንኙነቶች ማጠናከር፡-
- ስለ ድሆች እና ስለ ተገለሉት ስለ አካል ጉዳተኞች መብት መቆም፡-
- ቤተ ክርስቲያን ምንም ጊዜ ጦርነትን እንደምትቃወም፣ በጠንካራ እና ግልጽ አቋሙ መሆኑን።
- የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እና ወጣቶች ለሲኖዶስ መርህን ለመረዳት ያላቸውን ጥያቄና ሃሳብ ለመስማት በመቀራረብ በመወያየት መፍትሔ መፈለግ፡-
- ነጻነት እና ኃላፊነት በቤተክርስቲያን እይታ መብትና ግዴታዎች .... በሚል ርዕሰ ጉዳዮች የቀረቡ ናቸው።

የቤተ ክርስቲያን የእምነት ጉዳዮች ላይ ያለውን ሥነ-መለኮታዊ፣ ሕገ-ቀኖናዊ እና ሐዋርያዊ እረኝነት ለማስቀጠል የነገረ-መለኮት እና የሕገ ቀኖና ሊቃውንት ለሲኖዶሳዊነት ትርጉም በመስጠት የበኩላቸውን ምሁራዊ አስተዋፅዖ አድርገዋል።

በዋናነት ሲኖዶሳዊነት በአብሮነት፣ በተሳትፎ እና ተልዕኮ የመኖር እና የኅብረት ምስክርነት መንገድ መሆኑን እውቅና መስጠት ነው። ቤተክርስቲያን ኩባንያ ወይም ፓርቲ አይደለችም፥ ኤጲስ ቆጶሳት የሮም 'አስተዳዳሪዎች' አይደሉም፣ ምእመናን የካህናት ውሳኔዎችን እና መመሪያዎችን ብቻ የሚያስፈጽሙ አካላት አይደሉም።

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድነት የሚመላለሱባት መንገድ ወይም ማደሪያ ናት። የመኖሯ ምክንያት በመዋቅሮች፣ በቢሮክራሲዎች ወይም በሥልጣን አስተዳደር ውስጥ ብቻ አይደለም። የአስተሳሰብ ለውጥ ይጠይቃል። ሲኖዶሳዊነትን እንደ ቢሮክራሲያዊ ተግባር እንዳንቆጥረው ይጠይቀናል፣ በአባትነት መንፈስ የሚተገበር እንጂ፣ በጥቂት ጥቃቅን የመዋቢያ ማሻሻያዎች የሚስተካከል ብቻ አይደለም። ይህ የሚያስከትላቸው መዘዞችን ሁሉ በቀላሉ ከመታገስ ይልቅ አብሮ የመሄድ ፍላጎት እንደገና እንድናገኝ ግድ ይላል። ቤተክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ምሪት በመስማት በዘመኑ የሚታዩትን ምልክቶች እየለየች ዘመኑን ትዋጃለች። ግራ የተጋባውን የዓለም ገጽታ እያረመች ሰላማችን የሆነውን ክርስቶስን ለዓለም የማወጅ ተልዕኮዋንና ጉዞዋን ትቀጥላለች።

በመጨረሻ ምዕመናን የእግዚአብሔር ቅዱስ ሕዝቦች የመሆን ፀጋ ስለተሰጠን ለሲኖዳሳዊነት መንፈስ አጥብቀን እንያዝ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታዩ ለውጦችን ወዲያው ማየት አይቻል ይሆናል። ምክንያቱም ለውጦች ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው እና መንፈስ ቅዱስም ልባችንን ሊለውጥ ጊዜ ያስፈልገዋል። በጥምቀት እና በሜሮን ምስጢራት በኩል የተቀበልነው የወንጌል ተልዕኮ ግዴታ ጥሎብናል ። እንደ ቤተ ክርስቲያን አባልነታችን ይህን ተልዕኮ በቁምስናዎች፣ በትናንሽ መንፈሳዊ ማኅበራት፣ በሀገረ ስብከት እና በሌሎች የጋራ አገልግሎቶች በኩል አብረን እንድንፈጽም ተጠርተኛል።

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**

## በሰው መሀል ብቸኛ

ሰዎች በዚህ ምድር ላይ ሚያስፈራቸው ብዙ ነገር አለ። ለምሳሌ፡- ጦርነት የእሳት አደጋ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ሞት፣ ድህነት፣ ውርደት ወዘተ... ከነዚህ ሁሉ በላይ ግን የብቸኝነት ፍርሃት በጣም አስፈሪ ነው። ብቸኛ ሰዎች ሁልጊዜ የተከፉና ሀዘንተኞች ናቸው።

የልብ ግልፅነት የላቸውም። የልብ ግልፅነት ከሌለ ደግሞ መጨነቅ ራስን ማግለልና ጤናን ወደ ማጣት ያደርሰናል።

**የብቸኝነት መንስኤዎች፡-** የብቸኝነት መንስኤዎች እንደየሰው ስሜትና ጠባይ ይለያያል።



**ከብዙ በጥቂቱ፡-**

1. በመከራ ውስጥ ያለ ብቸኝነት፡- ይህ በችግርና በመከራ ውስጥ ስንሆን የሚሰጠን ብቸኝነት ነው።
2. በመገለል ውስጥ ያለ ብቸኝነት፡- በኑሮ ደረጃቸው አይዞህ ባይ ወገንና ዘመድ በማጣታቸው፣ በበሽታ በመያዛቸው፣ ባላቸው የዘርና የቀለም ልዩነት የተነሳ ሰዎች ራሳቸውን ያገላሉ፤ በሰዎችም ይገለላሉ።
3. በሐዘን ውስጥ ያለ ብቸኝነት፡- ይህ በሐዘንና በትካዜ የሚመጣ የልብ መሰበር ነው። የምትወዱትና አለኝ የምትሉትን ሰው በሞት በተነጠቃችሁ ጊዜ የሚመጣ የውስጥ ቁስል ነው።
4. በሰው መሀል በቸኛ ገንዘብ ሞልቶ ቢተርፋቸውም ፍቅርን ደስታንና እውነተኛ ወዳጅ ሊገዛላቸው ያልቻለ ባለሀብቶች።

ምንጭ - ስኬታማ የፍቅር ሕይወት (Successful Life of Love) በመምህር ዳንኤል ዓለሙ

ምሥጋና ካነበቡት ላካፈሉን! አቶ ፍቃደ አረዳ ( ወልቂጤ / እምድብር ሀገረስብከት )

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የሴቶችና ቤተሰብ ጉዳይ ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

‹‹... እነዚህ ከሚወዱኝ ይበልጥ ትወደኛለህን?...›› (ዮሐ.21፡15)

## 16ኛው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ...

ከገፅ 1 የዞረ

ርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቺስኮስ 16ኛውን የብፁዓን ጳጳሳት ጠቅላላ ጉባኤ ሁለተኛ ምዕራፍ ማክሰኞ መስከረም 22 ቀን 2017 ዓ. ም. ባስጀመሩበት ዕለት ባስተላለፉት መልዕክት፥ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ላይ ያላትን የሰላም እና የይቅር ባይነት ተልእኮዋን ለመወጣት በመንፈስ ቅዱስ የምትመራ ትሑት እና ሲኖዶሳዊት መሆን እንዳለባት በማሳሰብ፥ ጉባኤው ከተጀመረበት ከመስከረም 30/2014 ዓ. ም. አንስቶ በተካሄደው የሲኖዶሳዊነት ጉዞ ላይ አስተንትነዋል።

ብፁዕነታቸው ከዚህም በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያን ከሐዋርያት ዘመን አንስቶ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያስቀመጠውን ተልእኮ ሳታቋርጥ በመወጣት ላይ እንደምትገኝ ለጉባኤው ተሳታፊዎች በማስታወስ፥ የቤተ ክርስቲያን ዋና ተልዕኮ ኢየሱስ ክርስቶስን ለዓለም በመመስከር ሰላምን እና እርቅን ማግኘት እንደሆነ አስገንዝበዋል።

ሲኖዶሱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የእያንዳንዱን ካቶሊካዊ አመለካከትን ለመለካት ያለመ የሶስት ዓመታት ምክክር ሲያደርግ የነበረ ሲሆን፥ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቺስኮስ በተለምዶ የጳጳሳት ጉባኤ የሚባለውን ለአንዳንድ ምእመናን ክፍት በማድረግ ከ368 ድምጽ ሰጪዎች ውስጥ ወደ 60 የሚጠጉ ሴቶችን በማካተት አሳትፈዋል።

ርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ጉባኤውን በይፋ ባስጀመሩበት መስዋዕተ ቅዳሴ ላይ ባስተላለፉት ቃለምዕዳን ቤተክርስቲያን በሲኖዶሳዊ መንገድ መጓዟን ስትቀጥል በጸሎት እና በመደማመጥ መንፈስ እንዲሆን ጥሪ አድርገዋል።

ቅዱስነታቸው በዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ የሕዝብን ድምፅ ለማዳመጥ እና እንደ ህፃናት እራሳችንን ትንሽ አድርገን በትሕትና እርስ በርስ መከባበር እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

በተጨማሪም ርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ለዓለም ሰላም እና ለሰው ልጅ አንድነት እንዲሆን ሰኞ መስከረም 27 ቀን 2017 ዓ.ም. የፆም እና የጸሎት ቀን እንዲሆን በማወጅ ተግባራዊም ተደርጓል። በዕለቱም ካቶሊካውያን በአሁኑ ወቅት በጦርነት፣ በረሀብ እና በተለያዩ አደጋ ውስጥ ያሉትን በማሰብ ጸሎት ተደርጓል።

ከመስከረም 22 እስከ ጥቅምት 17 ቀን 2017 ዓ.ም. በተካሄደው የሲኖዶሱ ጉባኤ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን በመወከል ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ሊቀጳጳሳት ዘካቶሊካውያን እና ብፁዕ አቡነ ማርቆስ የጅማ ቦንጋ ሀገረስብከት ጳጳስ ተገኝተዋል።

የሲኖዶስ ጠቅላላ ጉባኤ፥ "መላው ቤተ ክርስቲያን ወደ ሙሉ የአንድነት ጎዳና እንዲጓዝ ለማድረግ ያለውን ጥልቅ ፍላጎት እና ምስክርነት ለመደገፍ እና አዲስ የክርስቲያኖች አንድነት ዘመን መጀመሪያን ለማክበር የተዘጋጀ እንደሆነም ተገልጿል።

በዚህም መሰረት ለአንድ ወር ሲካሄድ የነበረው 16ኛው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የብጹአን ጳጳሳት ሲኖዶስ እሁድ ጥቅምት 17 ቀን 2017 ዓ.ም. በቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቺስኮስ በመሩት የመዝጊያ መስዋዕተ ቅዳሴ ተጠናቋል።

ቅዱስነታቸው ከሦስት ዓመታት በፊት የተጀመረውን የሲኖዶስ ጉዞ በሃገራት ደረጃ፣ በክልላዊና አህጉራዊ ስብሰባዎች ተጀምሮ በ2016 ዓ.ም. ጥቅምት ወር በቫቲካን በተደረገው ስብሰባ ቀጥሎ፣ በያዝነው ዓመት ጥቅምት ወር ላይ በመጠናቀቁ በጋራ ስለተደረገው ጉዞ እግዚአብሔርን አመስግነዋል።

ርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቺስኮስ በጳጳሳት ሲኖዶስ ማጠቃለያ ቅዳሴ ላይ እንደ በርጠሜዎስ እንድንሆን እና 'አይነ ስውርነታችንን ለጌታ አደራ' እንድንል እንዲሁም 'ከጌታዋ ጋር በዓለም ጎዳና የምትመላለስ ሚሲዮናዊት ቤተክርስያን እንድንሆን' አሳስበዋል።

የሲኖዶሱን ውጤት ለምዕመናን ይፋ የሚደረግ ሲሆን ለተግባራዊነቱም ጳጳሳት ከመላው የእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር በመሆን አብረው በክርስቶስ ደስታ እንዲጓዙ ጥሪ አቅርበዋል።

በካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን የብፁዓን ጳጳሳት ጉባኤን እንደ ጎርጎሮሳውያኑ በ1965 የመሠረቱት የቀድሞው ርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ቅዱስ ጳውሎስ ስድስተኛ እንደ ነበሩ ይታወቃል።

## ...ክቡር አባ ኀበዝአየሁ...

ከገፅ 1 የዞረ

ዕጩ ጳጳስ ክቡር አባ ኀበዛየው ጌታቸው ይልማ በኦሮሚያ ክልል ዶዶላ (ባሌ ዞን) በተባለ ቦታ እ.አ.አ በታኅሣሥ 4 ቀን 1978 ዓ.ም ተወለዱ። በጅማ የግብርና ዩኒቨርሲቲ የግብርና ትምህርታቸውን ተከታትለው ያጠናቀቁ ሲሆን በመቀጠልም በአዲስ አበባ በሚገኘው ካፑቺን ፍራንችስካዊያን ኢንስቲትዩት የፍልስፍና እና ነገረ-መለኮት ትምህርት ተምረው አጠናቀዋል። ከሮማ ጳጳሳዊ ኡርባኒያና ዩኒቨርሲቲ በፍልስፍና ዲፕሎማ እና በነገረ መለኮት የመጀመሪያ ዲግሪ አግኝተዋል። ዕጩ ጳጳስ ክቡር አባ ኀበዛየው ጌታቸው እ.አ.አ በጥር 16 ቀን 2005 ዓ.ም ማዕረገ ክህነት ተቀብለዋል።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የኃላፊነት ቦታዎች በመያዝ ተጨማሪ ሐዋርያዊ እና ማሕበራዊ ተግባራትንአከናውነዋል።የመቂሰበካጳኃፊእና የወጣቶች አስተባባሪ (እ.አ.አ 2004-2005)፣ ምክትል ዋና ጸሐፊ፣ ከዚያም የመቂ የካቶሊክ ጽሕፈት ቤት ዋና ጸሐፊ (እ.አ.አ 2006-2009)፥ በዱብሊን በሚገኘው የኪሜጅ ልማት ጥናት ማዕከል በልማት ጥናት የማስተሬት ድግሪ እና ከሜይኖዝ ቅዱስ ፓትሪክ ጳጳሳዊ ዩኒቨርሲቲ በሥነ መለኮት የዶክትሬት ዲግሪ (በካቶሊክ ማህበራዊ አስተምህሮ፥ እ.አ.አ 2009-2015)። ከፍተኛ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው እ.አ.አ ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ የመቂ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ጸኃፊ እና በሀገረ ስብከቱ ሥር የሚተዳደረው ካሪታስ (የመቂ ካቶሊካዊ ጽሕፈት ቤት) ሥራ አስኪያጅ ሆነው አገልግለዋል።

የኢትዮጵያ ካቶሊክ ጳጳሳት ጉባኤ ደስታውን እየገለጸ ለክቡር አባ ኀበዝአየሁ ጌታቸው የተባረከ የአገልግሎት ዘመን እንዲሆንላቸው ይመኛል፡፡

# ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ የ14 ካቶሊካውያን ሰማዕታትን ቅድስና አወጁ

አባ ማኑኤል ሩይዝ ሎፔዝ እና ሰባቱ አጋሮቹ ፍራንሲስካውያን ወንድሞቹ፣ ወንድማማቾቹ ፍራንሲስ፣ ሙቲ እና ራፋኤል ማስሳብኪ፣ አባ ጆሴፍ አላማኖ፣ ሲስተር ማሪ ሊዮኒ ፓራዲስ እና ሲስተር ኤሌና ጊራ፣ በርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ ጥቅምት 10, 2017 ዓ.ም ቅድስናቸው ታውጇል።

ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት በዓለም የተልዕኮ ቀን በቅዱስ ጴጥሮስ አደባባይ ባሳረጉት መስዋዕተ ቅዳሴ ላይ ባደረጉት ንግግር፣ "እነዚህ አዲስ ቅዱሳን የኢየሱስን መንገድ ኖረዋል፡ አገልግለዋል።

አገልግሎታቸው ዓለማዊ ምኞታቸውንና የሥልጣን ረሃባቸውን አልመገበም፤ ይልቁንም ራሳቸውን የወንድሞቻቸውና የእህቶቻቸው አገልጋዮች፣ በችግር የጸኑ፣ እስከ መጨረሻም ለጋስ ሆነዋል። " ሲሉ ተናግረዋል።

ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት የቅዱሳኑ ምስክርነት ክርስቲያኖች ኢየሱስን ለማገልገል ያቀረበውን ግብዣ እንዲታዘዙ የሚጋብዝ እንጂ ክብርን እንዲፈልጉ አይደለም ብለዋል።

ለኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ባለውለታ የሆነው እና የኮንሰላታ ማህበር መሥራች ቅዱስ ጆሴፍ አላማኖ በማሰብ ከኢትዮጵያ ብፁዓን ጳጳሳት፣ የማህበሩ የአባቶች እና የእህቶች ገዳም አለቆች እና በጣልያን ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ካህናት እና ምዕመናን ተገኝተዋል።

## ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት...

ከገፅ 1 የዞረ

አባ ተስፋዬ ታደሰ ዘማኅበረ ኮምቦኒ በመስከረም 12, 1962 ዓ.ም. ( 22/09/1969 እ.ኤ.አ.) በሐረር ከተማ የተወለዱ ሲሆን ከተወለዱ ከጥቂት ወራት በኋላ ወደ ቤተሰባቸው የመኖሪያ ከተማ ወደ አዲስ አበባ መጡ። በአዲስ አበባ ከ 1ኛ እስከ 8ኛ በሰፈራቸው በነበሩት ትምህርት ቤቶች በምሥራቅና በነጻነት ብርሃን ትምህርት ቤቶች የተማሩ ሲሆን: ከ9ኛ ክፍል እስከ 12ኛ በቦሌ አጠቃላይ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተምረዋል። በአዲስ አበባ የመድኃኔ ዓለም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ወጣት ማኅበር አባል እያሉ: አሥራ ሁለተኛ ክፍል ከጨረሱ በኋላ: በ1979 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ባለው የኮምቦኒ ዘርዓ ክህነት ገቡ። በካፑቺን ፍራንሲስካውያን የፍልስፍናና የነገረ መለኰት ተቋም የፍልስፍና ትምህርታቸውን ተከታትለዋል።

ከዚያም በአዋሳ ከተማ በማኅበረ ኮምቦኒ ተመክሮ አድርገው በሚያዝያ 23: 1983 ዓ.ም ከሌሎች ወንድሞች ጋር የመጀመሪያ መሃላቸውን አደረጉ። ከዚያም ወደ ሮም ከተማ ለነገረ መለኮት ትምህርት ተልከው በግርጐርያን ዮኒቨርሲቲ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል: ከዚያም በዛው በሮም ባለ የቤተክርስቲያን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሰለ ሌላ እምነቶች በተለይ ሰለ እስልምና ሃይማኖት የድህረ ምረቃ ተጨማሪ ትምህርታቸውን የጀመሩ ሲሆን:

በሮም ከተማ በጥቅምት 22:1987 የመጨረሻ መሃላቸውን አድርገዋል። በታህሳስ 28:1987 በሮም ከረዳት ጳጳስ ክሌመንቴ ሪቫ እጅ ማዕረገ ድቁናን ተቀብለዋል: ከዚያም ወደሀገራቸው ተመልሰው ከብፁዕ አባታችን ካርዲናል ጳውሎስ ጻድዋ እጅ ማዕረግ ክህነትን በቁምስናቸው በመድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በነሐሴ 20:1987 ተቀብለዋል: ከክህነታቸው በኋላ ወደ ካይሮ ከዚያም ወደ ሮም ተልከው የጀመሩትን ትምህርትን ቀጥለዋል። ከዚያም ወደ ሱዳን ተመድበው በካርቱም ከ 1990-1993 ዓ.ም. በሐዋርያዊ ሥራ አገልግለዋል። ከዚያም ወደ ሮም ተመልሰው የድህረ ምረቃ ትምህርታቸውን አጠናቀዋል። ከዚያም ወደ ሀገራቸው ተመልሰው ለሁለት ዓመት ያህል በአዋሳ ሀገረ ስብከት ባሉ ሁለት ቁምስናዎች በሃሮ ዋቶ ጉጂና በቱሎ ሲዳማ የሐዋርያዊ ሥራና የትምህርት ቤት አገልግሎት ሰጥተዋል።

ከዚያም ወደ ሮም ተልከው በሳሌዝያውያን ዮኒቨርሲቲ ሰለዘርዓ ክህነት የሕንፀት አገልግሎት አጭር ኮርስ አድርገው ጉለሌ ባለው የማኅበረ ኮምቦኒ ዘርዓ ክህነት አገልግሎት ሰጥተዋል። በተጓዳኝ በጉለሌ ፍራንሲስካውያን የፍልስፍና የነገረ መለኰት ተቋም አስተምረዋል።

ከ 1994-1997 በኢትዮጵያ የማኅበረ ኮምቦኒ አለቃ አማካሪ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን: ይሄንም አገልግሎት እየሰጡ ሳሉ በ1998 በኢትዮጵያ የማኅበረ ኮምቦኒ አለቃ ሆነው እንዲያገለግሉ የተመረጡ ሲሆን ከሶስት ዓመት አገልግሎት በኋላ እንደገና ተመርጠው ሁለተኛ ዙር እያገለገሉ ሳሉ በተጓዳኝ የኢትዮጵያ የካቶሊክ ገዳማዊ ማኅበራት አለቆች ጉባዔ ሊቀመንበር ሆነው አገልግለዋል። አገልግሎታቸውን መስጠት እየቀጠሉ በሮም በነበረው ጠቅላላ ጉባዔ በጥቅምት 2002 የኮምቦኒ ማኅበር ጠቅላይ አለቃ አማካሪ ሆነው ተመረጡ። በመስከረም 2008 በሮም በነበረው ጠቅላላ ጉባዔ የኮምቦኒ ማኅበር ጠቅላይ አለቃ ሆነው ተመረጡ። በሰኔ 2014 እንደገና ጠቅላይ አለቃ ሆነው ተመረጡ። በሮም የማኅበራትና የገዳማት ጠቅላይ አለቆች ኅብረት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ሆነው ለሶስት ዓመት ያገለገሉ ሲሆን በኅብረቱ ስም በተለያዩ አገልግሎቶች የተሳተፉ ሲሆን ባለፉት ሶስት ዓመታት ሰለሲኖዳዊ የቤተክርስቲያን ተልኮ የሲኖዶስ ልዑክ ሆነው ተሳትፈዋል።

# በሀረርጌ ጭሮ ከተማ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ተመረቀ

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በሀረር ሀገረስብከት በያቦዶ ጎጃላ ወረዳ ንፁህ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክት ጥቅምት 19 ቀን 2017 ዓ.ም ለምረቃ በቅቷል። ሲ አር ኤስ (CRS) ፣ የሀረር ሀገረስብከት የልማት ጽ/ቤት እና የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ በጋራ በመሆን ለፕሮጀክቱ መሳካት የበኩላቸውን አድርገዋል።

ፕሮጀክቱን ሰርቶ ለማጠናቀቅ ከ 3 ወራት በታች እንዲሁም የውሃ ማጠራቀሚያውን ለመሥራት 15 ቀናትን እንደፈጀ እና 36.8 ሚሊየን ብር የገንዘብ ፍጆታን እንደነበረው የገለፁት ዶክተር በላይ አለማየሁ በአካባቢው የመጠጥ ውሃ እንደሚያስፈልግ በመረዳት የአካባቢው ሁኔታ እና መንገድ ሳይበግረን ፕሮጀክቱን ሰርተን አጠናቀናል። እናም ይህ ፕሮጀክት ለአካባቢው ሰዎች ትልቅ ዕረፍት ነው በማለት ተናግረዋል።

በዋዜማው የሀረር ሀገረስብከት ጽ/ቤት የልማት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ጎሳ መንግስቱ ስለ ጽ/ቤቱ ዓላማ እና ራዕይ ሪፖርት ያቀረቡ ሲሆን በሀረር ሀገረስብከት ውስጥ የተሰሩ ልማታዊ ሥራዎችን ለማሳየት የኤግዚቢሽን አውደ-ርዕይ ቀርቧል።

በዕለቱም የሀረር ሀገረስብከት ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አንጄሎ ፣ ክቡር አባ ከተማ አስፋው የኢትዮጵያ የጳጳሳት ጉባኤ ጸኃፊ፣ ካህናት፣ ከፍተኛ የመንግስት ኃላፊዎች ፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች እና የአካባቢው ነዋሪዎች ተገኝተው የሪቫን መቁረጥ ሥነ-ሥርዓት ተከናውኗል።

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከሶሻል ሪሃብሊቴሽን ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**"ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ መሞቱ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" (ሮም.5፡8)**

# ብፁዕ ወቅዱስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ መልዕክት ለወጣቶች

(ቅዱስ አባታችን ለ39ኛው የዓለም የወጣቶች ቀን ያስተላለፉት መልዕክት)

<<ጌታን በመተማመን የሚጠባበቁ ... ይሮጣሉ፤ አይታክቱም>> (ትንቢተ ኢሳያስ 40፡31)

የተወደዳችሁ ወጣቶች ሆይ!

ባለፈው አመት ወደ ኢዮቤልዩ ያደረግነው የተስፋ ጉዞአችንን የጀመርነው የቅዱስ ጳውሎስን "በተስፋ ደስ ይበላችሁ"(ሮሜ 12፡12) በሚለው ቃል ላይ በማሰላሰል ነበር። በቀጣይ ለሚኖረን የኢዮቤልዩ ንግደት (2017/2018) ለመዘጋጀት እንዲረዳን በዚህ ዓመት ከትንቢተ ኢሳያስ መልዕክት በመውሰድ እናስተነትናለን ፡- <<ጌታን በመተማመን የሚጠባበቁ ... ይሮጣሉ፤ አይታክቱም። (ኢሳ 40፡31) እነዚህ ቃላቶች የመጽናናት መጽሐፍት ተብለው ከሚጠሩት (ት. ኢሳያስ 40-50) የእሥራኤላውያንን በባቢሎን የግዞት ዘመን ማብቃቱን እና የአዲስ ተስፋ ጅማሬና የእግዚአብሔር ልጆች እንደገና መወለድን ከሚያበስረው መጽሐፍ ነው(ኢሳ 40፡3)።

አሁን የምንኖርበት ጊዜ በብዙ ውጣውረዶች የተሞላ በመሆኑ እንድንዝል እና ወደፊታችንን በሙሉ ተስፋ እንዳንመለከት ይከለክለናል፡- የጦርነት ሀዘን፣ ማህበራዊ ፍትህ መጓደል፣ እኩልነት አለመስፈን፣ ረሃብ፣ የሰው ልጆች እና የተፈጥሮ አለአግባብ መበዝበዝ። አብዛኛውን ጊዜ በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ከፍተኛውን ዋጋ የምትከፍሉት ወጣቶች ናችሁ። የወደፊቱን ሁኔታ እርግጠኛ መሆን አለመቻሉን ትረዳላችሁ እናም ሕልማችሁ ወደ የት እንደሚመራችሁ እርግጠኞች አይደላችሁም። በዚህ ሁኔታ በስልቹነትና በድብርት/በድባቴ/ እንደታሰሩ እስረኞች በመሆን ያለ ተስፋ ለመኖር ትፈተናላችሁ እንዲሁም አደገኛና አጥፊ ወደሆኑ ጠባዮች ትሳባላችሁ።በዚህ ምክንያት ውድ ወጣቶች ሆይ ልክ ለእሥራኤላውያን በባቢሎን እንደሆነላቸው የተስፋ መልዕክት ወደ እናንተ እንዲደርስ እፈልጋለሁ። ዛሬም እግዚአብሔር በፊታችሁ ጎዳናውን እየከፈተላችሁ ነው፤ በተስፋና በደስታ ትጓዙበትም ዘንድ ይጋብዛችኋል፡

## 1. የሕይወት ንግደት እና ተግዳሮቶቹ

ነቢዩ ኢሳያስ "ሳይደክሙ ስለመጓዝ" ይናገራል። እስኪ ስለእነዚህ መጓዝ እና ድካም ስለተባሉት ሁለት እውነታዎች እናስተንትን፡

ሕይወታችን ንግደት ነው፣ ከማንነታችን አልፈን እንድንሄድ የሚገፋን ጉዞ፣ ደስታን የመፈለግ ጉዞ። በተለይ የክርስቲያን ሕይወት ወደ መዳኛችን እና የሁሉም ጥሩ ነገሮች ሁሉ ፍጻሜ ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር የሚደረግ ንግደት ነው። በዚህ ጉዞ ላይ የሕይወት ግባችን፣ ስኬቶቻችን ቁሳዊ ነገሮች ብቻ ከሆኑ ከመጀመርያው ደስታ እና እርካታ በኋላ ድጋሚ እንራባቸዋለን፣ ሌላ አዲስ መሻትን እንመኛለን። እንዲህም ሆኖ ነፍሳችንን ሙሉ በሙሉ አያረኳትም፣ ምክንያቱም እኛ የተፈጠርነው ውስን ባልሆነው አምላክ ነው። በዚህም ምክንያት ወሰን የሌለውን ከአእምሮ በላይ የሆነውን (አምላክ) የመመኘት፡ ከደረስንበት ከፍ ወደሚለው እስክንደርስ ድረስ ያለማቋረጥ እንድንፈልግ የሚያደርገን አብሮን የተፈጠረ ፍላጎት አለ። የመሻገር/የመተላለፍ ውስጣዊ መሻት፣ የማያቋርጥ ትልልቅ ህልሞችን የማሳካት ተነሳሽነት አለን። ለዚህ ነው ደጋግሜ "ሕይወትን ከበረንዳ/ከሰገነት መመልከት" ለእናንተ ለወጣቶች በቂ አይደለም የምላችሁ።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ጉዞአችንን በጉጉት እየሄድን በአንድ ወቅት ድካም መሰማቱ የተለመደ ነው። አንዳንድ ጊዜ ባሉብን የማህበራዊ ግፊቶች በትምህርታችን፣ በሥራችን ወይም በግል የሕይወት ጉዞ ልንደርስባቸው ሰለምንፈልጋቸው ሁኔታዎች ስናስብ ጭንቀት እና ውስጣዊ ድካም ይሰማናል። በዚህ በባዶ "እንቅስቃሴ" ውስጥ ከአንዱ ነገር ወደ ሌላው እየሮጥን ስንኖር የተወሰነ የተስፋ መቁረጥ ስሜት ይፈጥራል እናም ቀናቶቻችንን በሺህ ነገሮች እንድንሞላው ያደርገናል። እናም በዚህ የተነሳ በቂ ነገር አለማድረጋችንና በቂነቱንም ለመለካት አለመቻላችን እንዲሰማን ያደርጋል፡ ይህ ድካም ብዙውን ጊዜ የሚመጣው ከግዴለሽነትና እርካታ ከማጣት ጋር ተያይዞ ሲሆን ይህም የሚያጠቃው እጃቸውን አጣምረው የሚቀመጡትን፡ ውሳኔ የማያደርጉትን፡ ኑሮን የማይጋፈጡትን፡ ከራሳቸው የምቾት ቀጣና መውጣት የማይፈልጉትን፡ ዓለምን ከርቀት በመመልከት በዓለም ላይ የሚፈርዱትን፡ ችግሮችን ለመፍታትና ኑሮን ለማሸነፍ የማይጥሩትንና ከሌሎች ጋር የማይተባበሩ ሰዎችን ነው። እንዲህ ዓይነቱ ድካም እርጥብ ሲሚንቶ ላይ የመቆም ዓይነት ነው፣ ውሎ አድሮ ይጠነክራል፣ ይከብደናል፣ ሽባ ያደርገናል እናም ወደ ፊት እንዳንሄድ ያግደናል። እኔ የምመርጠው ‹‹ድካም›› የመንቀሳቀስ ፍላጎታቸውን በመግታት የቆሙ ሰዎችን ድካም ሳይሆን፡ ቢደክሙም እንኳ መጓዛቸውን/መንቀሳቀሳቸውን/ ያላቋረጡ ሰዎች ድካምን ነው። ለዚህ ድካም መፍትሄው ፀጥ ብሎ በመቆም ማረፍ ሳይሆን ተነስቶ የተስፋ ተጓዥ (ነጋድያን) መሆን ነው።እናንተን የምጋብዛችሁ በተስፋ እንድትጓዙ ነው።

በተስፋ ተመላለሱ! ተስፋ ድካምን ሁሉ እያንዳንዱን ቀውስና ጭንቀትን ሁሉ ያሸንፋል። ተስፋ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ስጦታ ስለሆነ ወደፊት ለመሄድ ትልቅ ጉልበት ይሆነናልግዚአብሔር ለመንገዳችን ብርሃንን እያበራ፣የመጨረሻውን ግብ እና አቅጣጫ በማሳየት ሕይወታችን ትርጉም እንዲኖረው ያደርጋል።ሐዋርያው ጳውሎስ በመልዕክቱ በስታዲየም ውስጥ የድል ሽልማቱን ለመቀበል በሚወዳደር አትሌት ምስል ይመስለዋል(1ኛ ቆሮ 9፡24) በስፖርታዊ ውድድሮች ውስጥ እንደ ተመልካች ሳይሆን እንደ ተወዳዳሪ አትሌት የተካፈላችሁ የመጨረሻዋ መስመር ላይ ለመድረስ ምን ያህን ውስጣዊ ጥንካሬን እንደሚጠይቅ ታውቁታላችሁ።

ተስፋ እግዚአብሔር በውስጣችን ያስቀመጠውና በውድድር ላይ እንድንጸና የሚያደርገን፡ አሁን ካሉብን ችግሮች ባሻገር እንድናይ የሚያስችለን፡ ወደ ዘላለማዊው ሕይወትና ወደ እርሱ (ወደ እግዚአብሔር) አንድነት ወደሚወስደን ግብ እንድንጓዝ የሚገፋፋን አዲስ ኃይል ነው። አንድ የሚያምር ግብ ካለ ፣ ሕይወት የመጨረሻ ትርጉም ካላት ፣ የማልመው ፣ የማቅደው እና የማሳካው ነገር የማይጠፋ ከሆነ ፣እንግዲያውስ እንቅፋቶችን እና ድካምን በማሸነፍ ያላማቋረጥ መጓዝ ተገቢ ነው ፣ ምክንያቱም የመጨረሻው ሽልማት ከመጠን በላይ ድንቅና ሊለካ የማይችል ነው!

## 2. የበረሃ ላይ ነጋዲያን

በሕይወት የንግደት ጉዞ ውስጥ ፈተናዎች መኖራቸው የማይቀር ነው። ቀደም ባሉት ጊዜያት ረዣዥም የንግደት ጉዞዎች ያካትቱ የነበሩት፡ የአየር ንብረት ለውጦችን መቋቋም ፣ አስደሳች ሜዳዎችን እና ቀዝቃዛ ደኖችን ማቋረጥ ብቻ ሣይሆን በበረዶ የተሸፈኑ ተራሮችን እና ደረቃማ በረሃዎችን መጋፈጥን ይጨምራል ። እሥራኤላውያን ከምድረ በዳ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲጓዙ እንደደከሙ ሁሉ፡ አማኞችም የህይወታቸው የንግደት ጉዞና ወደመጨረሻው ግባቸው የሚያደርጉት ጉዞ አድካሚ መሆኑ ግልጽ ነው፤ እናም ለሁላችሁ የእምነትን ስጦታ ለተቀበላችሁ፡ እግዚአብሔር በመካከላችን ሲገኝ እና ቅርባችን መሆኑ ሲሰማን ደስ እንደሚለን ሁሉ የራቀን ሲመስለን የሚሰማን ስሜት ሌላ ነው። በመጀመሪያ ጊዜ ወደ ትምህርት ወይም ወደ ሥራ አለም የገባንበት ጊዜ ፣ በትዳር ሕይወት፣ በክህነት ሕይወት ወይም በምንኩስና ኑሮ ክርስቶስን ለመከተል የነበረን የመጀመሪያው የጋለ ፍላጎት/ጉጉት/ በችግር ሊታጀብ ይችላል። ይህም ሕይወትን በምድረ በዳ አስቸጋሪ ጉዞ ያስመስለዋል። ነገር ግን እነዚያ የችግር ጊዜያት የባከኑ ወይም ከንቱ አይደሉም፡ ምክንያቱም አስፈላጊ የሆኑ የምናድግባቸው ጊዜዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ተስፋ የጸዳባቸው ጊዜያት ናቸው! በችግር ጊዜ፣ ብዙ የውሸት "ተስፋዎች"፣ ለልባችን በጣም ትንሽ የሆኑ ተስፋዎች፣ትርጉማቸው እየጠፉ ይሄዳሉ። እነሱ ለሚሆኑት ነገር ይገለጣሉ፣እኛም የቅዠት ዓለም ውስጥ ሳንገባ መሰረታዊ የሕይወት ጥያቄዎችን ለመጋፈጥ ብቻችንን መሆናችንን እንገነዘባለን። እናም በእነዚያ ጊዜያት እያንዳንዳችን ራሳችንን እንዲህ ብለን መጠየቅ እንችላለን ሕይወቴን መሰረት ያደረግኩባቸው ተስፋዎች ምንድን ናቸው? እውነተኛ ተስፋዎች ናቸው ወይንስ ተአምራት?

በእነዚያ ጊዜያት ጌታ አይተወንም። እንደ አባት ወደ እኛ ቀርቦ በጉዞአችንኃይላችንን የሚያድስ እንጀራ ያለማቋረጥ ይሰጠናል። በምድረ በዳ ለነበሩት ሰዎች መና እንደሰጣቸው እናስታውስ (ዘጸ.16)ለነቢዩ ኤልያስም ደክሞና ተስፋ ቆርጦ በነበረበትጊዜ ሁለት ጊዜ ዳቦና ውኃ በማቅረብ የእግዚአብሔር ተራራ" ወዳለበት "እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት እንዲሄድ እንዳደረገው ልብ እንበል።(1ኛ ነገ. 19፡3-8)። በእነዚያ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች ውስጥ እንደምናገኘው በጉዞአችን ጠንክረን እንድንጓዝ የሚያደርገን፡ ለጉዞአችን እውነተኛ ስንቅና እውነተኛው መና የሆነው ውድ ስጦታ ቅዱስ ቁርባን መሆኑን የቤተክርስቲያን እምነት ይገልጻል። ብፁዕ ካርሎ አኩቲስ እንዳለው፣ ቅዱስ ቁርባን ወደ መንግስተ ሰማይ የሚወስድ መንገድ ነው። ካርሎ በቅዱስ ቁርባን የሚገኘውን ኢየሱስ እለት በእለት ማግኘት ዋና ተግባሩ አደረገ። በዚህ ዓይነት እኛም ከጌታ ጋር በመሆን ያለመታከት መጓዝ እንችላለን፣ ምክንያቱም እርሱ ከእኛ ጋር ይጓዛልና (ማቴ.28፡20)። በመተባበር፣ ሳንታክት ልንመላለስ እንችላለን፣ እርሱ ከእኛ ጋር እየሄደ ነው (ማቴ.28፡20)። ሁላችሁም የቅዱስ ቁርባንን ታላቅ ስጦታ እንደገና ታገኙት ዘንድ አበረታታችኋለሁ!

እንግዲያውስ በዚህ ዓለም በምናደርገው በማይቀረው የድካም ጊዜ ውስጥእንደ ኢየሱስ ማረፍ እና በኢየሱስ ማረፍን እንማር። ደቀ መዛሙርቱን ከተልዕኳቸው ከተመለሱ በኋላ እንዲያርፉ ነገራቸው (ማር. 6፡31)። እንዲሁም አንተ ዕረፍት እንደሚያስፈልግህ ያውቃል፣ ይኸውም የአካል ዕረፍት, የመዝናኛ ጊዜ, ከጓደኞች ጋር አብሮ መደሰት, የስፖርት ጊዜ እና የመተኛት ጊዜ አስፈላጊነቱን ጌታ ስለሚያውቅ እንድታርፍ ይፈልጋል። ነገር ግን ብዙዎች የሚሹት ጥቂቶች ብቻ የሚያገኙት ጥልቅ የሆነ ዕረፍት አለ ይኸውም የነፍስ ዕረፍት ነው፣ ይህም የሚገኘው በክርስቶስ ብቻ ነው። የውስጥ ድካማችሁ በሙሉ፡ እንዲህ በሚላችሁ በጌታ ኢየሱስ ማረፍ እንደምትችሉ እወቁ፡ "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ" (ማቴ 11፡28)፣ ስለዚህ የጉዞው ድካም ሲጫጫናችሁ ወደ ኢየሱስ ተመለሱ፣ በእርሱ ማረፍን ተማሩ እናም ከእርሱ ጋር ኑሩ፣ ምክንያቱም "ጌታን ተስፋ የሚያደርጉ... ይሮጣሉ አይታክቱም" (ኢሳ 40፡31)።

## 3. ከጎብኚነት ወደ መንፈሳዊ ተጓዥነት

ውድ ወጣቶች፣ ለሕይወት ጉዞአችሁ እንድትነሱ፣ ሕይወትን በፍቅር እንድትመለከቷት እና የእግዚአብሔርን ፍቅር እንድትፈልጉ እጋብዛችኋለሁ። እኔ የምመክራችሁ እንደ መንፈሳዊ ተጓዦች(እንደ ነጋዲያን) እንጂ እንደ ቱሪስት ብቻ አትሁኑ በማለት ነው። የቦታዎችን እና የመንገዶችን እውነተኛ ትርጉማቸውን ሳትረዱ የላይኛውን ውበት ብቻ አይታችሁ፣ የግል ምስላችሁን "ሰልፊ" ተነስታችሁ ብቻ የምትሄዱ ጎብኚዎች አትሁኑ። ቱሪስቶችም እንዲህ ያደርጋሉና። መንፈሳዊ ተጓዦች ግን በተለየ ሁኔታ በሚሄዱባቸው ስፍራዎች ሁሉ እራሳቸውን በጥልቀት ከቦታው ጋር ያቆራኛሉ፣ የሚተላለፉ መልዕክቶችን ያዳምጣሉ፣ እነዚህንም መልዕክቶች ለሕይወታቸው ደስታ እና ሙላት እንዲሆንላቸው ያደርጋሉ። የኢዮቤልዩ መንፈሳዊ ጉዞ (ንግደት) ሁላችንም ለተጠራንበት ለመጨረሻው መዳረሻ (ለዘለዓለማዊ ሕይወት) የውስጣዊ ጉዞ ውጫዊ ምልክት ነው።

በዚህ አመለካከት ሁላችንም ለኢዮቤልዩ ዓመት እንዘጋጅ። ብዙዎቻችሁ ወደ ሮም መንፈሳዊ ጉዞን በማድረግ በሚከፈቱት የምህረት በሮች እንደምታልፉ ተስፋ አደርጋለሁ። ነገር ግን ይህንን ማድረግ ባትችሉ በየሀገረስብከታችሁ በሚገኙ ቤተክርስቲያኖች እና የመንፈሳዊ ንግደት ቦታዎች በመሄድ እምነታችሁን እንድታጸኑ እና በእግዚአብሔር የምህረት በሮች እንድታልፉ እጋብዛለሁ። ይህ የኢዩቤልዩ ንግደት እያንዳንዳችን < sየመዳናችን በር > ከሆነው ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር እውነተኛ የሆነ የግል ግንኙነት የምናዳብርበት እንዲሆን ምኞቴ ነው።

ወደ ገፅ 9 ዞሯል

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከትምህርት ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

"ስላደረገልን መልካም ነገር ሁሉ ጌታን ከማመስገን በቀር ምን እንመልስለታለን" (መዝ. 116፡12)

VATICAN MEDIA

# የቫቲካን ሚዲያ ገጽ

# የደኅንነት አዋጅ ማኅበራዊና ኅብረተሰባዊ ውጤቶች

**የደኅንነት አዋጅ ግልጽ የሆነ ማኅበራዊ ይዘት አለው። የወንጌል ማዕከላዊ ሃሳብ ማኅበራዊ ሕይወትና ከሌሎች ጋር መገናኘት ነው። የመጀመሪያው አዋጅ ይዘት በፍቅር ላይ የተመሠረተ ግብረ ገባዊ አንድምታ አለው።**

**ክፍል 3**

### እምነትን ለኅብረተሰብ መግለጽና ዝግጁ መሆን

ወንዶችና ሴቶችን ሁሉ በማያልቅ ፍቅር በሚወደው አብ ማመን ማለት «እርሱ ለእነርሱ የማያልቅ ክብር እንደሚያጎናጽፋቸው» መገንዘብ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ ሰብአዊ ሥጋችንን ወሰደ ማለት እያንዳንዱ ሰው ወደ እግዚአብሔር ልብ ቀረበ ማለት ነው። ኢየሱስ ስለ እኛ ደሙን እንዳፈሰሰ ማመን ለእያንዳንዱ ሰው ክብርን ስለሚያጎናጽፈው የማያልቅ ፍቅሩ ያለንን ጥርጣሬ ሁሉ ያስወግዳል። መዳናችን ማህበራዊ ገጽታ አለው፤ ይህም የሆነው «እግዚአብሔር በክርስቶስ እያንዳንዱን ግለሰብ ብቻ ሳይሆን፣ በሰዎች መካከል ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት ሁሉ ስለሚያድን ነው።» መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ሰው ውስጥ እየሠራ መሆኑን ማመን ማለት ወደ እያንዳንዱ የሰው ሁኔታና ማህበራዊ ግንኙነት ሁሉ ለመግባት እንደሚሻ መገንዘብ ነው። «መንፈስ ቅዱስ፣ ለመለኮታዊ ሃሳብ የተገባ፣ እጅግ ውስብስብና ምስጢራዊ የሆኑ የሰብአዊ ጉዳይ ቋጠሮዎችን እንኳ መፍታት የሚችል የማያልቅ የፈጠራ ችሎታ አለው»። ስብከተ ወንጌል ከዚህ ነጻ ከሚያወጣ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጋር መተባበር ይጠበቅበታል። የሥላሴ ምሥጢር በዚያ መለኮታዊ ሱታፌ አምሳል የተፈጠርን መሆናችንን ያሳስበናል፤ ስለዚህ፣ በራሳችን ጥረት ብቻ ጽድቅ ወይም ደኅንነት ልናገኝ አንችልም። ከወንጌል ማዕከላዊ አስተሳሰብ ስንነሣ በስብከተ ወንጌልና በሰብአዊ ዕድገት መካከል ያለውን ጥልቅ ግንኙነት እናያለን፤ ይህም በማንኛውም የስብከተ ወንጌል ሥራ መገለጥና መዳበር ይኖርበታል። የእግዚአብሔርን ፍቅር እንድንቀበልና የእርሱ ስጦታ በሆነው በዚያው ፍቅር እርሱን እንድንወድ የሚጠራን የመጀመሪያው ትእዛዝ በሕይወታችንና በሥራችን ውስጥ ቀዳሚና መሠረታዊ የሆነ የሌሎች ሰዎችን በጎ የመመኘት፣ የመሻትና የመጠበቅ ምላሽ ያፈልቃል።

የደኅንነትን መልእክት በመቀበልና በእውነተኛ የወንድማማችነት ፍቅር መካከል ያለው ይህ የማይበጠስ ትስስር ውጤቶቻቸውን ሁሉ በአድናቆት ለመቀበል በሚገባ ማሰላሰል በሚያስፈልጉን አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ውስጥ ተገልጾ ይገኛል። መልእክቱ ብዙውን ጊዜ እንዳለ የምንቀበለውና በሕይወታችንና በማኅበረሰቦቻችን ውስጥ ያለው ተጨባጭ ውጤት ምን እንደሆነ ሳይረጋገጥ እንዲሁ የሚደጋገም ነው። ይህ ደግሞ በወንድማማችነትና በፍትህ ወንጌል ለመኖር ያለንን አድናቆት፣ ጉጉትና ፍላጎት የሚያጠፋ ስለሆነ አደገኛና ጎጂ ነው። ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ለእያንዳንዳችን ተጨማሪ የሰብአዊነት መገለጫ እንደሆኑ የእግዚአብሔር ቃል ያስተምረናል። «ከእነዚህ አነስተኛ ከሆኑት ወንድሞቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት ለእኔ እንዳደረጋችሁት ነው» (ማቴ.25፡40) ይላልና። ለሌሎች ሰዎች ያለን አያያዝ ወደር የሌለው ገጽታ አለው፣ «በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል» (ማቴ.7፡2) ተብሎአልና። እግዚአብሔር ካሳየን ምሕረትም ጋር የሚመሳሰል ነው፤ «አባታችሁ ርኅሩኅ እንደሆነ እናንተም ርኅሩኆች ሁኑ። አትፍረዱ፣ አይፈረድባችሁም፤ አትኰንኑ አትኰነኑም፤ ይቅር በሉ፣ ይቅር ትባላላችሁ። ስጡ ይሰጣችኋል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርባችኋል» (ሉቃ.6፡36-38) ተብሎ ተጽፎአልና። እነዚህ ምንባቦች «ከራሳችን ወጥተን ወደ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ለመሄድ» ፍጹም ቅድሚያ መስጠት እንዳለብን በግልጽ ያስረዳሉ። ይህም ከሁለቱ ታላላቅ ትእዛዞች አንዱን የያዘውን የግብረ ገብ መመዘኛና ለእግዚአብሔር ነጻ ስጦታ ምላሽ የሆነውን መንፈሳዊ ዕድገት ለይቶ የማወቅን ምልክት የሚያሳይ ነው። በዚህ ምክንያት «የፍቅር ሥራ የቤተክርስቲያን ተልእኮ አካልና የሕልውናዋ ዋና መገለጫ ነው» ቤተክርስቲያን በባህርይዋ ልዑክ ናት፤ በውጤታማ የፍቅር ሥራ በሚያውቅ፣ በሚረዳና በሚያሳድግ ርኅራኄ የተሞላች ናት።

### መንግሥተ ሰማይና ፈተናዎቹ

ወንጌል ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግላዊ ግንኙነት ብቻ የሚያሳይ አለመሆኑን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በግልጽ ያስረዳል። ለእግዚአብሔር የምንሰጠው ፍቅራዊ ምላሽም ለተቸገሩ ግለሰቦች የሚደረጉ ትናንሽ ግላዊ እንቅስቃሴዎች ጥርቅም፣ «የፍቅር ሥራ ዝርዝር» ወይም የ**ኅሊና**ችንን ሸክም ለማቃለል ብቻ የሚደረጉ ሥራዎች ተደርጎ መታየት የለበትም። ወንጌል ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የሚናገር ነው (ንጽ.ሉቃ.4፡43)፤ በዓለማችን ስለሚነግሠው የእግዚአብሔር ፍቅር የሚያስረዳ ነው። እርሱ በእኛ ውስጥ እስከነገሠ ድረስ የኅብረተሰብ ሕይወት ለአጠቃላይ ወንድማማችነት፣ ፍትህ፣ ሰላምና ክብር መሠረት ይሆናል። ስለዚህ፣ ክርስቲያናዊ ስብከትም ሆነ ሕይወት በህብረተሰብ ላይ አንድምታ ሊኖረው ይገባል። እኛ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንሻለን፣ «ከሁሉ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል» (ማቴ.6፡33) ተብሎአልና። የኢየሱስ ተልዕኮ የአባቱን መንግሥት ማወጅ ነው፤ እርሱም «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች» (ማቴ.10፡7) ብለው የምሥራቹን ቃል እንዲሰብኩ ደቀ መዛሙርቱን አዘዘ።

አስቀድሞ በመካከላችን የሚገኘውና እየሰፋ ያለው የእግዚአብሔር መንግሥት ባለንበት ደረጃ ሁሉ ይመለከተናል፣ ለይቶ የማወቅ መርሆንም ያሳስበናል። ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጳውሎስ 6ኛ ይህ መርሆ «በሰዎች ሁሉና በሙሉ ሰው» እውነተኛ ዕድገት ላይ ያተኮረ መሆን እንዳለበት አስረድተዋል። «የወንጌል ስብከት በወንጌልና በሰው ልጅ ተጨባጭ ግላዊና ማኅበራዊ ሕይወት መካከል ያለውን የማያቋርጥ ውህደት ካላገናዘበ በቀር ሙሉ ሊሆን እንደማይችል» እናውቃለን። ይህም በወንጌል ውስጥ ያለ የአጠቃላይነት መርሆ ነው፤ ምክንያቱም አብ የሰውን ሁሉ ደኅንነት ይመኛል፣ የማዳን ዕቅዱም «በሰማይም፣ በምድርም ያሉትን ነገሮች ሁሉ ራስ በሆነው በክርስቶስ ሥር ለመጠቅለል ነው» (ኤፌ.1፡10)። የእኛ ተልእኮ «ወደ ዓለም ሁሉ መሄድ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ መስበክ» (ማር.16፡15) ነው። ምክንያቱም «ፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ በናፍቆት ይጠባበቃል» (ሮሜ.8፡19)። እዚህ ላይ «ፍጥረት» የሚለው ቃል የሰውን ሕይወት ሁለንተናዊ ገጽታ ያመለክታል፤ በመሆኑም «የኢየሱስ ክርስቶስን የምሥራች ቃል የመስበክ ተልእኮ አጠቃላይ መዳረሻ ግብ አለው። የፍቅር ተልእኮው የሕልውናን ሁሉ ገጽታ፣ ሁሉን ግለሰቦች፣ ሁሉን ማኅበራዊ ሕይወትና ሁሉንም ሕዝቦች ያጠቃልላል። ማንም ሰው ለእርሱ ባዕድ አይሆንም»። የሚገለጠውን የእግዚአብሔር መንግሥት የሚሻ እውነተኛ ክርስቲያናዊ ተስፋ ሁል ጊዜ ታሪክ ይሠራል።

***ምንጭ፡*** *ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቸስኮስ የወንጌል ደስታ በሚል አርዕስት በዛሬው ዓለም ወንጌልን ስለመስበክ ለጳጳሳት፣ ለካህናት፣ ለደናግላን እና ለምዕመናን ይፋ ካደረጉት ሐዋርያዊ ምክር ከአንቀጽ 177-181 ላይ የተወሰደ።*

# ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ተቋማት ኮንፈረንስ በአዲስ አበባ ተካሄደ

ኢትዮጵያ ያዘጋጀችው ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ተቋማት ኮንፈረንስ ጥቅምት 25 እና 26 ቀን 2017 ዓ.ም በአዲስ አበባ የተደረገ ሲሆን ከ16 አገራት የተወጣጡ የሃይማኖት አባቶችና የተቋማት መሪዎች ተሳትፈውበታል።

ይህንን ዓለም አቀፍ የሃይማኖት ተቋማት ኮንፈረንስ የኢፌዲሪ ፕሬዝዳንት አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ፣ የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ አንዱዓለም እና የመሀመድ ቢን ዛይድ ዩኒቨርሲቲ ቻንስለር ዶክተር ከሊፋ ሙባረክ ከፍተዋል።

የኢፌድሪ ክቡር ፕሬዚዳንት ታዬ አጽቀሥላሴ በመድረኩ ላይ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ኢትዮጵያ ለዘመናት በሃይማኖቶች መካከል መቻቻልንና አብሮ መኖርን ያሳየች ፣ ክርስትናንና እስልምናን ቀድማ የተቀበለች ሀገር መሆኗን በመጥቀስ በሀገሪቱ ያለውን የሃይማኖቶች መቻቻል አብራርተዋል።

የኢትዮጲያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን በመወከል የተገኙት ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ ሱራፌል "ሁላችንም ከየትኛውም የሃይማኖት ተቋም ብንመጣም የጋራ እሴቶቻችን ከልዩነቶቻችን ማለፍ አለባቸው" በማለት "ለአገር ሰላም ግንባታ በተከፈተ ልብና አዕምሮ መሥራትና በአንድነት መንፈስ መጓዝ አለብን" በማለት ጥሪ አቅርበዋል።

ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ወክለው በመድረኩ የተገኙት የኢትዮጲያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ የቦርድ ሰብሳቢ አቡነ ጎርጎርዮስ "ሰላም አገርን ከጥፋት ሕዝብን ከመከራ ማትረፍ የሚችል በመሆኑ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስለሰላም ደጋግማ ታስተምራለች፣ ታውጃለችም" ብለዋል።

"በሃይማኖቶች መካከል የሚደረግ ውይይት እጅግ አስፈላጊ ነው" ያሉት የኢትዮጲያ የሀይማኖት ተቋማት ጉባኤ የበላይ ጠባቂ ሼህ ሀጂ ኢብራሂም ቱፋ "ዓለማችን ካለችበት ብጥብጥና ግጭት እንድትወጣ በጋራ ሆነን አበክረን መሥራት አለብን" ብለዋል።

*ምንጭ : ሰላም ካቶሊክ ቲቪ*

**ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከፍትህና ሰላም ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው።**

**"በሁሉ ነገር እናመስግን፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእናንተ ይህ ነውና" (1ተሰ. 5፡18)**



በክቡር አባ አብነት አበበ
ዘማኅበረ ልኡካን/ ላዛሪስት

# ይበልጥ መውደድ

## ስምዖን ሆይ..‹‹...ይበልጥ ትወደኛለህን?›› (ዮሐ.21፡15)

ሰዎች ከሚፈልጓቸው ነገሮች ውስጥ አንዱና ዋነኛው በሌሎች ዘንድ መወደድን ነው። ለመወደድ ደግሞ አስቀድሞ መውደድ ያስፈልጋል፤ ይህ *‹መውደድ› የሚገለጸው በተግባር ነውና (ዮሐ. 14፡15) እግዚአብሔር ዓለምን እጅግ ስለ ወደደ አንድያ ልጁን ሰጠ እንደሚለው (ዮሐ. 3፡16)* እኛም ፈጣሪ አምላካችን ስለወደደን አዲስ ዓመትን ሰጠን እንላለን። ይህ ስጦታ (ይህ አውደ ዓመት) ፍቅሩን ከሚገልጥባቸው ስጦታዎች አንዱ ነው። በመሆኑም ከተደረገልን አንጻር የወደደንን አምላክ መልሰን ብንወድ አይገርምም ምክንያቱም ፍቅር ማለት እኛ እግዚአብሔርን ስለወደድነው ሳይሆን እርሱ ስለወደደን... ነውና (1ዮሐ. 4፡10)። ስለዚህ ዘንድሮም 365 ቀናትን የሰጠን አምላክ ልክ ስምዖን ጴጥሮስን ‹‹እነዚህ ከሚወዱኝ ይበልጥ ትወደኛለህን?›› (ዮሐ.21፡15) ብሎ እንደጠየቀው እኛንም ‹አምና› ከወደዳችሁኝ ይበልጥ ትወዱኛላችሁን ብሎ ይጠይቀናል።

እንደምንወደው የሚያውቅ አምላክ የዘንድሮው ፍቅራችን ከአምናው በልጦ ማየት ይሻል፤እርሱን በማፍቀር እንድናድግ ይፈልጋል። ለፍቅሩ ምላሽ ለመስጠት ‹በቅድሚያ› እንደሚወደን ማወቅና ፍቅሩን በትህትናና በምስጋና መቀበል ያስፈልጋል። እግዚአብሔር ምን ያህል እንደሚወደን የመጽሐፍ ቅዱስን ምስክርነት በጥቂቱ እንመልከት።

እግዚአብሔር ሲወደን እንዲህ ነው፣ እናት ልጆችዋን ከምትወዳቸው በላይ ይወደናል (ኢሳ. 49፡15)፣ ልጆቼ ይለናል (ዮሐ. 21፡5) መርጦናል (ዮሐ. 15፡16)፣ ያውቀናል (ዮሐ.13፡18) ከመረጣቸው ጋር ለዘላለም ይሆናል (ራእ. 3፡20)፣ እስከ እርጅናችን ይጠነቀቅልናል (ኢሳ. 46፡4)፣ ፍቅሩ ዘላለማዊ ነው (ኢሳ. 54፡10፣55፡3፣ 50፡1) ፍቅሩ ያድናል (ዮሐ. 3፡16፤ ኢሳ. 50፡2፣59፡1፤ 43፡1-4)፣ ፍቅሩ ይቅር ባይ ነው (ዮሐ. 8፡10-11። ማቴ 18፡27)፤ ፍቅሩ ስለእኛ እቅድ ያለው ፍቅር ነው (ኤር. 29፡11)፣ አፍቃሪ አባታችን ፍቅሩን ለእያንዳንዳችን የሚገልጽ አባት ነው (ኢሳ. 49፡26) ለጥያቄአችን መልስ የሚሰጥ ፍቅር ነው (ማቴ. 7፡7-12)፣ ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ መሞቱ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል (ሮም.5፡8) አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ መውደዱን ያሳያል (ዮሐ. 3፡16)፣ ስለሚወደን መንፈስ ቅዱስን ይሰጠናል (ሉቃ. 11፡13፤ ሮም. 5፡5)፤ በፍቅሩ ልጆቹ አድርጎናል (1ዮሐ. 3፡1፤ ሮም 8፡15-16)።

እግዚአብሔር እንደሚወደን ማወቅ በራሱ ለራሳችን ክብርን እንድንሰጥና ራሳችንን እንድንወድ ያግዘናል ምክንያቱም ማንም ሰው አይወደኝም (የሚወደኝ ሰው የለም) የሚል እምነት ካለን ራሳችንን አንወድም፣ ለራሳችን የምንሰጠው ዋጋ ዝቅ ስለሚል ለራሳችን ክብርን አንሰጥም። ራሳችንን ካልወደድንና ካላከበርን ሌሎችን መውደድና ማክበር ያስቸግራል፤ ስለዚህ ሳንወደው የወደደንን አምላክ እያመሰገንን ከአምናው ይልቅ ‹ዘንድሮ› ፍቅራችን ጨምሮ እንወደው ዘንድ በሚከተሉት አራት መንገዶች መውደዳችንን እንግለጽለት፣ ይኸውም ለእርሱ ይበልጥ ጊዜ በመስጠት፡ እርሱን ይበልጥ ለማወቅ በመትጋት እርሱን መታዘዛችንን በማብዛትና ሰዎችን ሁሉ ያለምክንያት በመውደድ ከአምናው በበለጠ እንደምንወደው እንግለጽለት።

### 1, ይበልጥ በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መሆን

ከምንወዳቸው ሰዎች ጋር መገናኘት ስንፈልግ ሁሌም ጊዜ እንደምናገኝ ሁሉ የወደደንን አምላክ ስንወደው ‹ከእርሱ ጋር ብቻ› የምንሆንበት የአብሮነት ጊዜ ያስፈልገናል። ስለዚህ ከአምናው ይበልጥ ዘንድሮ ከእርሱ ጋር የምንሆንበትን የጸሎት ጊዜ እናመቻች። ከእርሱ ጋር በሚኖረን ጊዜ አምላካችንን ስለማንነቱ እናመስግነው ስለ ኃጢአታችን ይቅርታውን እንለምን ስላደረገልን እናመስግን ስለሚያስፈልገን ነገር ደግሞ እንለምነው።

- **ይበልጥ ማምለክ**

በእግዚአብሔር ፊት ስንሆን እርሱ ፈጣሪያችንና አዳኛችን ጌታችንና አፍቃሪያችን መሆኑን በማመን ሰዎች መሆናችንን ሳንዘነጋ በትህትና እርሱን እናመስግን ስለማንነቱ ውዳሴን እናቅርብለት። ‹‹እግዚአብሔር ታላቅ ነው። ከፍተኛ ምስጋናም የሚገባው ነው። ታላቅነቱም ሰው ከሚያስተውለው በላይ ነው›› (መዝ. 145፡3)። ‹‹ኃያል አምላክ ነው፤ ከአማልክት ሁሉ በላይ የሆነ ታላቅ ንጉስ ነው፤ ምድርን በሙሉ ይገዛል፤ የፈጠረውን ይቆጣጠራል፤ አምላካችን ነው፤ እኛም እርሱ የሚጠነቀቅልን ሕዝቦቹና የሚያሰማራን በጎቹ ነን›› (መዝ. 95፡1-7)።

- **ይበልጥ ይቅር ማለት**

ለጸሎት ስንቆም ስንንበረከክ ወይም በመሬት ላይ ስንቀመጥ በፊታችን ባለው አምላክ ፊት መሆኑን ስናስብ ትንሽነታችን ኃጢአተኛነታችን እንመልከት። ‹‹ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፣ እውነትም በእኛ ዘንድ የለም። ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን የታመነና ጻድቅ ነው፣ ከዓመጻም ሁሉ ያነጻናል፣ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን፣ ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም›› (1ዮሐ.1፡8-10)። ስለዚህ በማሰብ በመናገር በማድረግ ተግባርህን ባለመፈጸም ብዙ ኃጢአት መሥራታችንን ለእግዚአብሔር እንናዘዝ፤ ስላሰብነው ክፋት፣ ስለተናገርነው ክፉ ቃል፣ ስለሰራነው ክፋትና መሥራት እየተገባን ስላልሰራነው መልካም ነገር በማስተንተን የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንለምን። እርሱ የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ አይንቅም (መዝ. 51፡19)። ኃጢአታችንን በግልጽ ለእርሱ ስናሳውቅ መተላለፋችንን ስንነግረው የኃጢአታችንን ሸክም ይተውልናል (መዝ. 32፡5)። በተጨማሪም የሰማዩ አባታችን ኃጢአታችንን ይቅር ይልልን ዘንድ የበደሉንን ሰዎች ይቅር እንበላቸው (ማር. 11፡25)። ከአምናው በበለጠ ይቅርታን በማድረግ ይቅርታን ከፈጣሪያችን እንለምን።

- **ይበልጥ ማመስገን**

ስለማንነቱ ውዳሴን የምናቀርብለት አምላክ ንስሐችንን ተቀብሎ ይቅር የሚል አምላክ ነውና ስለተቀበልነው ምህረትና ስማይነገር ስጦታው ልናመሰግነው ይገባል። እግዚአብሔር አምላክ ስላደረገልን እያደረገልን ስላለው ነገርና ወደፊትም ስለሚያደርግልን ነገር ሁሉ ከአምናው የበለጠ ምስጋና እናቅርብለት። ትናንት ያደረገልንን በማስታወስ ዛሬም እያደረገልን ያለውን ነገር በመመልከትና ወደፊት ሊያደርግልን ስላቀደው መልካም ነገር በማሰብ የሚገባውን ምስጋና እንስጠው። ‹‹ምስጋናን የሚሰዋ ያከብረኛል›› እንዳለው (መዝ.50፡23) ከአምናው ይበልጥ በማመስገን እናክብረው። ‹ስላደረገልን መልካም ነገር ሁሉ ጌታን ከማመስገን በቀር ምን እንመልስለታለን (መዝ. 116፡12) ስለዚህ በሁሉ ነገር እናመስግን፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ይህ ነውና›› (1ተሰ. 5፡18)።

- **ይበልጥ መለመን**

እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ማኅበረሰብ ብዙ የሚያስፈልጉን ነገሮች አሉ፤ ለምኑ ይሰጣችኋል ይላልና ዛሬ ለጎደሉን ነገሮች ምክንያቱ የእኛ ያለመጸለይ ችግር ነው፤ ስለዚህ አቅማችንን አውቀን ድህነታችንን ተቀብለን የሚያስፈልገንን ይሰጠን ዘንድ የሰማዩ አባታችንን ከአምናው ይበልጥ እንለምነው እርሱ ምን እንደሚያስፈልገን ያውቃል ስለ እኛ ያስባል የሚያስጨንቀንን ሁሉ በእርሱ ላይ እንጣል (1ጴጥ.5፡7)። ለቤተሰቦቻችን፣ ለጓደኞቻችን፣ ለዘመዶቻችን ለሥራ ባልደረቦቻችን፣ ለመምህራን ለአሰልጣኞች ለሃኪሞችና በችግር ጊዜ ቀድመው ለሚደርሱ፤ ለቤተክርስቲያን እረኞች፤ እግዚአብሔርን በመምሰልና በተገባ አካሄድ ሁሉ ጸጥታ የሰፈነበትና ሰላማዊ የሆነ ሕይወት እንዲኖረን ስለ ነገሥታትና በከፍተኛ ሥልጣን ላይ ስላሉ ሁሉ (1ጢሞ. 2፡1-2) ለታመሙ እና ለድሆች በተለይም ልዩ ትኩረት ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንጸልይ፤ በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችንን ልናስታውቅ እንጂ በምንም ዓይነት ነገር ልንጨነቅ አይገባም (ፊል. 4፡6)።

### 2, የሚወደንን አምላክ ይበልጥ ማወቅ

አንድን ሰው ስንወድ ስለዚያ ሰው ይበልጥ ለማወቅ እንደምንጥር ሁሉ የወደድነውን አምላክ ይበልጥ ለማወቅ ቅዱስ መጽሐፍን እናንብብ፣ ቅዱስ ጀሮም እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስን የማያውቅ ክርስቶስን አያውቅምና። እንዲሁም ስለክርስቶስ ማንነት ይበልጥ ለመረዳት እርሱን በጸሎት እንጠይቅ።

ካርዲናል ፉልተን ሺን ሲናገሩ እንዲህ ብለው ነበር፤ ዓለማችን በጣም የሚያስፈልጋት ዋናው ነገር እውቀት ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር አዋቂዎችን በላከላት ነበር፤ በጣም የሚያስፈልጋት ትክኖሎጂ ቢሆን ኖሮ፡ እግዚአብሔር ሳይንቲስት በላከላት ነበር፣ በጣም ያስፈለጋት ገንዘብ ቢሆን ኖሮ ኢኮኖሚስት በላከላት ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የላከላት የዓለም መድኃኒት የሆነውን አዳኙን ልጁ ኢየሱስን ነው፤ ምክንያቱም ዓለማችንእጅግ በጣም የሚያስፈልጋት ነገር የኃጢአት ይቅርታና ከኃጢአት ነጻ መውጣት ነውና።

ስለዚህ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ የሆነው ኢየሱስን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ይበልጥ ማወቅ (ዮሐ. 1፡29) ኃጢአተኞች ለሆንን ‹ሰዎች› ለተባልን ፍጡሮች በሙሉ ተገቢና አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም የዘላለም ሕይወት ማለት እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆነውን እግዚአብሔርንና የላከውን ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነውና (ዮሐ. 17፡3)። በመሆኑም እርሱን ይበልጥ እንድናውቅ የጥበብንና የመገለጥን መንፈስ እንዲሰጠን እንለምነው (ኤፌ. 1፡17)። እርሱ የፈጠረን እንድናውቀው እንድንወደው ትዕዛዙን እንድንፈጽም ይህንንም በማድረግ በዚህ ምድር ተባርከን መንግስተ ሰማይ እንድንገባ ነው።እናም ከአምናው ይልቅ ዘንድሮ ይበልጥ እንቅረበውና ይበልጥ እንወቀው። ያን ጊዜ የአንድ አባት ልጆች መሆናችን ይበልጥ እንረዳለን።


### 3, ትእዛዙን ይበልጥ መጠበቅ

‹‹የምትወዱኝ ከሆነ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ›› እንደሚለው (ዮሐ. 14፡15) ፍቅር የሚገለጸው በተግባር ነው። እኛም እግዚአብሔርን እንደምንወድ ፈቃዱን በማድረግ እርሱ የሚወደውን ነገር በመውደድና የሚጠላውን ክፉ ነገር በመጥላት ከአምናው ይልቅ ዘንድሮ ትእዛዙን ይበልጥ እንጠብቅ። ያሳለፍነውን ዓመት (2017 ዓመተ ምህረትን) ስናስብ የምናመሰግንበት ምክንያት እንዳለን ሁሉ ስለኃጢአታችን ይቅርታን ከፈጣሪያችንና ከበደልናቸው ሰዎች የምንጠይቅበት ብዙ ምክንያት መኖሩን ኅሊናችን ያውቀዋል። ራስ ወዳድነታችን በዝቶና መጨካከናችን ጎልቶ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ አንዳችን በሌላችን ላይ የፈጸምናቸው እኩይ ተግባራት (ባንፈጽማቸው እንኳ ሲፈጸሙ እያየን እንዳላየን ሰምተን እንዳልሰማን ላሳለፍናቸው ጊዜያት) የፈጠሩብን የውስጥ ስብራት ይበቃልና ካለፈው ስህተታችን ተምረን በተሰጠን አዲስ ዓመት ክፉ ተግባራትን ለመጸየፍና ለማውገዝ በምትኩም የብዙ መልካም ሥራዎች ተካፋይ ለመሆን እንዘጋጅ። ‹‹ሰው ሆይ መልካም ምን እንደሆነ ላንተ ነግሮሃል፣ ፍትህን እንድታደርግ፣ ምህረትን እንድትወድና ከአምላክህም ጋር በትሕትና እንድትሄድ ካልሆነ በቀር ጌታ ከአንተ የሚፈልገው ነገር ምንድነው›› እንደሚለው (ሚክ.6፡8)። ይቅርታን በመውደድ ከአምናው ይበልጥ ዘንድሮ ለእውነትና ለፍትህ በመቆም ለእግዚአብሔር ፈቃድና ለቃሉ ታዛዦች እንሁን(ሮም. 12፡2)።

ወደ ገፅ 11 ዞሯል

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ሐዋርያዊ ሥራዎች ኮሚሽን ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**“ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖርሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል” (ዮሐ. 14፡15-16)**



# ፍቅርና

በየወሩ ፡ መዠመሪያ ፡ እሑድ ፡ የሚወጣ ፤ ካቶሊካዊ ፡ ዜና ፤

አዲስ ፡ አበባ ፡ ካቶሊካዊ ፡ ቤተ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፤—

ቍ. ፩ መስከረም ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ. ም.



**ቤተ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን**
**አዲስ አበባ**

ምዕመናኖቻችን መንፈሳዊ ጥቅምን የሚያገኙበት ፍቅርና ሰላም በሚል ስም የተሰየመው ይህ ካቶሊካዊ ወርኃዊ ጋዜጣ ተቋቁሞ ሥራውን ሲጀምር በማየታችን ደስታችን ትልቅ ነው።

አሁኑ ጊዜ መጀመሪያ ቦታ የያዙት የመገናኛ ዘዴዎች እንደ ጋዜጣና ሌሎች ጽሑፎች ራዲዮ ሲኒማና ቴሌቪዥን እግዚአብሔር በኪነ ጥበቡ ከፈጠራቸው ሥነ ፍጥረቶች በሰው አእምሮ ብልሐትና መመራመር የተገኙ የአምላክ ስጦታዎች ናቸው።

የእነዚህ የመገናኛ ዘዴዎች ቀዳማዊ ዓላማ የእግዚአብሔር ስጦታዎች እንደመሆናቸው መጠን ለኅብረተ ሰቡ ጠቃሚ አገልግሎትን መስጠት ነው። ጠቃሚ አገልግሎት የሚፈጽሙት በሰው የሰረፀው የማወቅ የመገናኘትና የመወያየት ፍላጎትን በማርካት እውነትን በማሰወቅን በማስፋፋት የወንድማማችነት መንፈስንም በማዳበር በኅብረተ ሰብ መካከል ርዕትና ሰላም የሚሰፍንበትን መንገድ በመፈለግ ነው።

በማኅተም ተባዝቶ የሚሰራጨው በሲኒማና በቴሌቪዥን የሚታየውና የሚሰማው ሁሉ የኅብረተ ሰብ ሕይወትን ለማነጽና ለማሻሻል ከመጥቀም ፋንታ ሞራልን የሚያንኳስስ በኅብረተ ሰብ መካከል ጥልን መለያየትን የሚፈጥር ሰላምን የሚነሳ ከሆነ ግን የመገናኛ ዘዴዎች ቀዳሚ ዓላማቸውን ስትዋል ከእግዚአብሔር የተሰጠው ጥበብ በከንቱ ባክነዋል ለማለት ያድደፍራል።

ይህ “ፍቅርና ሰላም” በሚል ስም የሚወጣው ወርኃዊ ጋዜጣ ምእመናኖቻችን በመንፈሳቸው የሚታነፁበት ጠቃሚ መሳሪያ እንዲሆን እንጠባበቃለን። ክርስቶስን በማስታወቅ የወንጌሉን ትምህርት በመዘርጋት የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያስፋፋ መንፈሳዊ መሳሪያ እንዲሆን ፍላጎታችን ነው።

ጋዜጣው የመገናኛ ዘዴ እንደመሆኑ መጠን ምእመናን “አነ ውእቱ ፍኖትኒ ወጽድቅ ወሕይወት እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ (ዮሐ. 14፡ -6) ከሚለው ከጌታ ክርስቶስ የሚገናኙበት መሳሪያ መሆን አለበት። በክርስቶስ እውነትና ሕይወትን እንዲሁም የድኅነታችውን መንገድ አግኝተው ምእመናን በክርስቶስ እርስ በርሳቸው ለመገናኘት በዚሁም እንደ አንድ የእግዚአብሔር ቤተ ሰብ ሆነው ለመኖር የሚረዳቸውና የሚያስረዳቸው መንፈሳዊ መሳሪያ ይሆን ዘንድ እንመኛለን።

ይህ ወርኃዊ ጋዜጣ ለምእመናኖቻችን መንፈሳዊ ጥቅም የሚዘጋጅ ነውና ምእመናን ድጋፋቸው እንዳይለየው ጥብቅ የሆነ አደራችንን ጥለንባቸዋል።

ጋዜጣው እንደ ስሙ በኅብረተ ሰቡ መካከል ፍቅርና ሰላምን አሰራጭቶ የሚጠበቅበትን ዓላማ እንዲያሟላ ልባዊ ምኞታችንን እንገልጻለን።

✠ አ. ዓሥራት ማርም የምሩ
ካቶ.ሊቀ ጳጳስ።

✠ አ. ጳውሎስ ጻድዋ
ረዳት ጳጳስ።




## በወቅቱ የነበሩት ጳጳሳት

- ብፁዕ ሊቀ ጳጳስት አቡነ አሥራት ማርያም የምሩ የአዲስ አበባ ሀገረ ሰብከት ሊቀ ጳጳስ
- ብፁዕ ካርዲናል ጳውሎስ ፃድዋ ረዳት ጳጳስ በነበሩት ወቅት ነው።
- ብፁዕ አቡነ ኃይለማርያም የአዲግራት ጳጳስ
- ብፁዕ አቡነ አብርሃ ፍራንሷ የአስመራ ጳጳስ
- ብፁዕ አቡነ ሉቃ ሜሊዚ ጳጳስ
- ብፁዕ አቡነ ኡርባኖስ የሐረር ጳጳስ
- ብፁዕ አቡነ ዶመኒኮ ማሪኖሲ የሶዶ ሆሳዕና ጳጳስ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጳጳስት ጉባኤ አባል የነበሩ

## በወቅቱ የአዲስ አበባ ቁምስናዎች

- ልደተማርያም ቁምስና አባ ዘካሪያስ / የአስመራ ጳጳስ የነበሩ/
- መድኃኔ ዓለም ቁምስና አባ ገብረማርያም አመንቴ
- ኪዳነ ምህረት ቁምስና አባ ቶማስ ጻዕሩ
- ቅዱስ ገብርኤል ቁምስና አባ ጴጥሮስ ካህሳይ
- ፍልሰተ ማርያም /ጽዮን ማርም / ቁምስና የላዛርስት አባቶች
- ቅዱስ ፍራንቼስኮስ ቁምስና ካፑቺን አባቶች
- ቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ፀሎት ሲታውን አባቶች ነበሩ።

ወቅቱ በኢትዮጵያ የመንግሥት ለውጥ የተጀመረበት ሲሆን የመንግሥትን አስተዳደርን ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳዳር /ደርግ/ የያዘበት ፤ የቀድሞ የዘውድ ከቦታው የተነሳበት ሲሆን የነበረውን አገዛዝ ባልተጨበጠ ተስፋ እና ምኖት በመግባት የተደረገ ዛሬ ለገባነው ያልተረጋጋ ሕይወት የዳረገን ጂማሬ ነበር።



**“ሰለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል” (2ቆሮ. 5:17)**

# የዓለም የወንጌል ተልእኮ ቀን

በጌታ ኢየሱስ የተወደዳችሁ ካቶሊካውያን ቤተሰብ ምእመናንና ወጣቶች ሁሉ እንኳን ለ2017 ዓ.ም የዓለም የወንጌል ተልእኮ ቀን አደረሳችሁ መልእክቴ በያላችሁበት ይድረሳችሁ።

እነሆ ዛሬ ጥቅምት 10 ቀን 2017 ዓ.ም. በምናከብረው የዓለም የተልእኮ ቀን ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ በመልእክታቸው ‹‹ሄዳችሁ ያገኛችሁትን ሁሉ ወደ ሠርጉ ጥሩ›› (ማቴ. 22፡9) በሚለው መሪ ቃል አማካኝነት ካቶሊካውያን ሁላችን የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሰዎች ሁሉ ለማድረስ እንድንሄድና ሁሉንም ወደ ፍቅሩ ገበታ እንጋብዝ ጥሪ ያቀርቡልናል፤ ለሰዎች ሁሉ የሚያስፈልጋቸው መድኃኒት የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነውና።

ወንጌልን የመስበክ ግዴታ

ወንጌልን እንድንሰብክ ጌታችን ኢየሱስ አዞናል (ማር. 16፡15) በመሆኑም ይህ ወንጌል ለሰው ሁሉ መሰበክ አለበት (ማር. 13፡10) ተጋባዥ ሰዎችም የተሰጣቸውን የመዳን ዕድል በመጠቀም፡ የሚድኑትና እውነት መንገድና ሕይወት የሆነውን አምላክ (ዮሐ. 14፡6) ወደ ማወቅ የሚመጡት (1ጢሞ.2፡4) እርሱ ብቻ አዳኝ የሆነውን ኢየሱስ (ሐ.ሥ. 4፡12) እንደ ግል አዳኛቸው ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበል የሚወስኑት እኛ ወንጌሉን ስንሰብክላቸው ነው። ስለዚህ ግድ በሚለን በክርስቶስ ፍቅር ተገፋፍተን (2ቆሮ. 5፡14) ሰውን ሁሉ ወደ ፍቅሩ ግብዣ እንጥራ።

## ለስብከተ ወንጌል መተባበር

በክርስቶስ በቤተክርስቲያንና በስብከተ ወንጌል መካከል ጥልቅ ትስስር ስላለ ለክርስቶስና ለቤተክርቲያኑ ታማኝ በመሆን ይህንን ወንጌል ከቤተክርስቲያን ጋር በመሆን በቤተክርስቲያን በኩል ከመንፈሳዊ አባቶቻችን ማለትም ከጳጳሳትና ከካህናት ጋር በመተባበርና ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ከሚያስተላልፉልን አስተምህሮ ጋር በማዋሀድ ሰዎችን ሁሉ ወደ ጌታ ማእድ፡ ማእከል ወደሆነው ወደ ቅዱስ ቁርባን እንጋብዛቸው።

ክርስቶስን ማእከል ያደረገ ስብከት

ተልእኮአችን ከኃጢአት በመራቅና የክርስቶስን መንፈስ በመላበስ ኢየሱስን ማእከል ያደረገ ወንጌል በመስበክ በንግግራችንና በተግባራችን ስለ ክርስቶስ መመስከርና ሰዎችን ሁሉ ወደ ፍቅሩ ገበታ መጋበዝ ነው። የወንጌሉ መልእክት ወደ ተጋበዙት ሰዎች (ወደ እያንዳንዳችንም ጭምር) ደረሰ ማለት የሚቻለው ግብዣውን በነጻነት ተቀብለው ቅዱስ ቃሉን በመስማትና የክርስቶስን ሥጋ እና ደሙን በመመገብ ሕይወታቸው ሲለወጥና ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍቅር ሌሎችን በማገልገል ሲገልጹ ነው።

## የወንጌሉ መልእክት ፍሬ ሀሳብ

ፍሬ እንድናፈራ ስለተሾምን፡ ሰዎችን ሁሉ ወደ ሠርጉ ግብዣ ስንጠራ በዋናነት እግዚአብሔር እንደሚወዳቸውና ስለ እነርሱ ሕይወት እቅድ እንዳለው እንንገራቸው(ኤር. 29፡11)፤ ነገር ግን ይህ እቅድ በኃጢአት ምክንያት መበላሸቱን ((ሮም. 5፡12) በዚህም ምክንያት ከፈጣሪያችን ጋር የነበረን ግንኙነት መቋረጡን፤ ይህንን ግንኙነት ለማስቀጠል ኢየሱስ ስለኃጢአታችን መሞቱን (ሮም. 5፡8)፤ በእኛና በአባቱ መካከል እንደ ድልድይ እንደሆነልንና ይህ የሞተልን አምላክ ከእያንዳንዳችን ምላሽ እንደሚፈልግ፣ ይህም ንስሐ በመግባት ከአምላካችን ጋር እንድንታረቅ የሚጋብዝ መሆኑን (ሐ.ሥ. 19፡18)፤ ኃጢአትን መናዘዝና መጠመቅ እንደሚገባ (ማቴ. 3፡6) በምስጢረ ጥምቀት አማካይነት የቤተክርስቲያን አባል መሆን እንደሚችሉና (1ቆሮ. 12፡13) በመጨረሻም ከተማሩ በኋላ የክርስቶስ ደቀመዝሙር እንደሚሆኑ መንገር ነው የእኛ ድርሻ (ማቴ. 28፡19-20)።

## የወንጌል ተልእኮው ፍሬአማ እንዲሆን

የምናገኛቸውን ሁሉ ወደ ሠርጉ ግብዣ በምንጠራበት ጊዜ የእግዚአብሔር መልእክተኞች መሆናችንን እናስታውስ። ሁልጊዜም በትህትና ቃሉን እንስበክ፤ በድፍረትም እንናገረው፤ በኑሮአችንም እንዲታይ እናድርግ በምንሄድበት ሁሉ አምላካችን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነውና። ሁሉን ነገር በሚያስተምረንና በሚያጽናናን በመንፈስ ቅዱስ እንተማመን፤ እንጸልይ፤ እንዘጋጅ፤ እግዚአብሔር ድንቅ ነገሮችና ተኣምራትን እንደሚያከናውን በእምነት እንጠብቅ። በጌታ እንደሰት፤ ተስፋም እናድርግ።

## ምስጋና ለሚሲዮናውያን

ቅዱስ አባታችን በመልአክታቸው ስለ ስብከተ ወንጌል ብለው ቤተሰባቸውንና አገራቸውን ትተው ወደ መላው ዓለም የሄዱትን ሚስዮናውያንን ያመሰግናሉ። እኔም የእሳቸውን አብነት በመከተል ወደ አገራችን ኢትዮጵያ መጥተው ያገለገሉና በማገልገል ላይ ያሉ ሚሲዮናውያንን ማመስገን ተገቢ መስሎ ታየኝ። ከወጣትነት እድሜያቸው እስከ እርጅናቸው ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ፡ ዘርና ቀለም፣ ኃይማኖትና ጎሳ ሣይለዩ ኢትዮጵያውያን ወንድም እህቶቻችንን በመንፈሳዊና በዓለማዊ እውቀት አስተምራችሁ ለቁም ነገር ያደረሳችሁ ሚስዮናውያን ካህናት አባቶቻችንና ሲስተሮች (እናቶቻችን) ክብርና ምስጋና ይድረሳችሁ።

በተለይም በአገራችን ኢትዮጵያ ከመቶ ዓመት በላይ ሕዝባችንን በቅንነትና በፍቅር ያገለገሉትንና በማገልገል ላይ ያሉትን የኮንሶላታ ሚሲዮናውያን አባቶችንና እናቶችን በልዩ ሁኔታ እናመሰግናቸዋለን፤ ምክንያቱም የወንጌል ተልእኮ ቀን በምናከብርበት ዕለት፡ በቫቲካን ቅድስናቸው ከታወጁት አገልጋዮች መካከል የኮንሶላታ ሚሲዮናዊያን መሥራች የሆኑት አባ ዮሴፍ አላማኖ አንዱ ናቸውና። ኮንሶላታዊያን ካህናትና ሲስተሮች እንኳን ደስ አላችሁ። የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን እና የብዙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሕይወት መለወጥ ምክንያት ሆናችኋልና ምስጋና ይገባችኋል። በእናንተ በኩል ብዙ መልካም ነገሮችን ያደረገልን አምላክ ዘወትር ይባረክ!

እናታችን አጽናኝዋ ማርያም በዘመናችን ለምናከናውነው የስብከተ ወንጌል ተልእኮ አማላጅነቷ አይለየን!

*አባ አብነት አበበ (ዘማኅበረ ልኡካን/ላዛሪስት)*
*በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን*
*የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት*
*የቤተሰብ የምእመናንና የወጣቶች ሐዋርያዊ አገልግሎት መምሪያ ዳይሬክተር*

# ስለ ሕፃናትና ተጋላጭ አዋቂዎች እንክብካቤና ጥበቃ/Safeguarding of Children and Vulnerable Adults/ ስልጠና ተሰጠ

ላለፉት አራት ቀናት ከጥቅምት 14 እስከ 17 ቀን 2017 ዓ.ም አዲስ አበባ በሚገኘው ቅዱስ ፍራንቺስኮስ የፍልስፍናና የነገረ መለኮት ተቋም ውስጥ ለካህናትና ለከፍተኛ ዘርዓ ክህነት ተማሪዎች (ሴሚናሪስቶች) ስለ ሕፃናትና ተጋላጭ አዋቂዎች እንክብካቤና ጥበቃ ስልጠና ተሰጠ።

ስልጠናው የተሰጠው ከናይሮቢ (ኬንያ) ከአሚሴያ ቢሮ በመጡ እንግዶች የአሚሴያ ሐዋርያዊ አገልግሎት ዋና ኃላፊ የነበሩና የአገልግሎት ጊዜያቸውን ጨርሰው በተሰናበቱት በክቡር አባ አማኑኤል ቺሞምቦ እና እሳቸውን በተኩዋቸው ክቡር አባ ፍሎረንስ ሩታይዋ፣ በአቶ ጆርጅ ቱኩና በወ/ሮ ፖሊን ዋንጅሩ ሲሆን በኢትዮጵያ ካቶሊክ ጳጳሳት ጉባኤ ጽ/ቤት በኩል ደግሞ ወ/ሮ መርሐዊት ስለ ሕፃናትና ተጋላጭ አዋቂዎች እንክብካቤና ጥበቃ ምንነት በማብራራት ቤተክርስቲያኒቷ በዚህ ዙሪያ እስካሁን ስለሰራቻቸውና በመሥራት ላይ ስላለችው ጉዳይ ጠቅለል ያለ መረጃ አቅርባለች።

ካህናት በተለይም የዘርዓ ክህነት ተማዎች የሚያዘጋጁ ካህናት የመጀመሪያውን ሁለት ቀናት ማለትም ሐሙስና ዓርብ ስልጠናውን የወሰዱ ሲሆን የዘርዓ ክህነት ተማሪዎች በተቋሙ የሚማሩ ሲስተሮች ደግሞ ስልጠናውን ቅዳሜና እሁድ ወስደዋል። ክቡር አባ ቺሞምቦ የእሁዱን መስዋእተ ቅዳሴ በመምራት ቃለ ምእዳን አሰምተዋል። በስብከታቸውም ጌታን ለመከተል መወሰን የግለሰቡ ምርጫ ሲሆን ምርጫው የሚያስከትለውን ነገር ለመቀበል መዘጋጀት ተገቢ ነው ብለዋል። ካህናቱ ሴሚናሪስቶችና ሲስተሮች በስልጠናው መደሰታቸውን ገልጠዋል።

ክቡር አባ አበራ ማኬቦ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ጳጳሳት ጉባኤ ጽ/ቤት ምክትል ዋና ጸሐፊና የሐዋርያዊ አገልግሎት ዋና ተጠሪ እንግዶቹንና ተሳታፊዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ ስልጠናውን በጸሎት የከፈቱ ሲሆን ክቡር አባ አብነት አበበ የቤተሰብ የምእመናንና የወጣቶች ሐዋርያዊ አገልግሎት አስተባባሪ ደግሞ ፕሮግራሙን በጸሎት ዘግተዋል።

# በነፍሳት ቀን የሙታን መታሰቢያ ጸሎት ተደረገ

ጥቅምት 23 ቀን 2017 ዓ.ም በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በበርካታ አገረ ስብከቶች እና ቁምስናዎች ለነፍሳት የመታሰቢያ ጸሎት ተደረገ። በአዲስ አበባም በቅዱስ ጴጥሮስ ወጳውሎስ መካነ መቃብር በርካታ ምዕመናን፣ ደናግላን፣ ወንድሞች እና ካህናት የተገኙ ሲሆን የመካነ መቃብር ጽዳት ተደርጎ ለሁሉ ጸሎት ተደርጎ ውሏል።

ምዕመናን በሞት ወደ ዘላለማዊ ሕይወት የቀደሟቸውን የሚያስቡበት ይህ ቀን በየዓመቱ ጥቅምት 23 የሚከበር ነው። በቅዱሳን ሁሉ በዓልን ተከትሎ የሙታን መታሰቢያ ይደረጋል። በዚህ ዕለት ሁላችን ወደ እግዚአብሔር እና ወደ ዘላለማዊ ቤታችን የምንሄድ፣ በዚህ እንግዶች ሆነን የምኖር መሆናችን የሚያስታውሰን ቀን ነው።

*ምንጭ : ሰላም ካቶሊክ ቲቪ*

# በመቂ ሀገረስብከት የካቴኪስቶች ሥልጠና መካሄድ ጀመረ

በመቂ ሀገረስብከት ከአሥር ቁምስናዎች ለተውጣጡ ካቴኪስቶች በጂጌሣ የካቴኪስቶች ማዕከል ሥልጠና ተሰጠ።

የመቂ ሀገረስብከት የሐዋርያዊ ሥራዎች አስተባባሪ ክቡር አባ ሙላቱ ሰብሮ ከአሥሩም ቁምስና ለመጡ ካቴኪስቶች የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር በማድረግ ሥልጠናው በይፋ ከፍተዋል።

በመክፈቻው መርሃ ግብር ላይ የተገኙት የመቂ ሀገረስብከት ጳጳስ ብፁዕ አቡነ አብርሃም ደስታ “ያለ ካቴኪስቶች በካህናት እና ደናግላን ብቻ ወንጌልን ማሰራጨት አይቻልም፤ ካቴኪስቶች የካህናት ቀኝ እጅ በመሆንና በመተባበር ወንጌልን ለሰው ሁሉ ማዳረስ እንደምትችሉ ቤተክርስቲያን ስለምታምን ይህንን ስልጠና አዘጋጅታለች” ሲሉ ተናግረዋል።

ክቡር አባ ሚሊዮን ማርዮ በበኩላቸው ሥልጠናው 3 ዓመት እንደሚወስድ እና ሥልጠናው የሚያካትታችውን የትምህርት ርዕሶች ካስረዱ በኃላ “ካቴኪስቶች የተመረጣችሁትና የተጠራችሁት በሰው ሳይሆን በእግዚአብሔር ስለሆነ ለዚህም ዓላማና ጥሪ ታማኞች መሆን አለባችሁ” ሲሉ አሳስበዋል።

3 ዓመት የሚወስደውን የካቴኪስቶች ስልጠናም ክቡር አባ ዋልታንጉስ ዮሴፍ የመጽሐፍ ቅዱስ መግቢያ ትምህርት በመስጠት ተጀምሯል።

*ምንጭ፡- የመቂ ሀገረስብከት ማህበራዊ ተግባቦት ክፍል*

**ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የሕፃናት እንክብካቤ እና ጥበቃ ቢሮ ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው**

**“ኃጢአታችንን በግልጽ ለእርሱ ስናሳውቅ መተላለፋችንን ስንነግረው የኃጢአታችንን ሸክም ይተውልናል” (መዝ. 32፡5)**

# የቃሉ ውበት

## “የማያፈቅር እግዚአብሔርን አያውቅም፥ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና” (1 ዮሐ 4፡ 8)

**ክቡር አባ ዳንኤል አሰፋ**

***ሥርጉት***፦ ስለ ፍቅር ብዙ ይባላል። እውነተኛውን እና የማስመሰልን ፍቅር እንዴት መለየት ይቻላል?

***ሳሙኤል***፦ የእናት ፍቅር ለምሳሌ ማስመሰል አለበት ማለት ያስቸግራል።

***ሥርጉት***፦ እሱማ የተፈጥሮ ፍቅር ነው። አውቆ፣ አቅዶ የሚያደርጉት ነገር አይደለም።

***ሳሙኤል***፦ አሁን ለምሳሌ ሰው ፍቅር ያዘኝ ሲል እኮ፣ አውቆና አቅዶ የሚያደርገው ነገር አይደለም። ስለዚህም ፍቅር ከስሜት ጋር በጣም የተሳሰረ ነገር ይመስለኛል።

***ሥርጉት***፦ ገና ሳታድግ ከአቅምህ በላይ ነው የምታስበው።

***ኀሊና***፦ እንዴ ምን ማለትሽ ነው። ***ሳሙኤል*** እኮ አድጓል። እኅቱ ስለሆንሽ እድገቱ አይታይሽም ይሆናል።

***ሥርጉት***፦ ቁመት ጨምሮአል፤ ነገር ግን ምን ያህል የሕይወት ልምድ ኖሮት ነው፣ ፍቅርን በስሜት የሚገልጠው።

***ሳሙኤል***፦ “ፍቅር ያዘኝ” ማለት፣ ፍቅር ስሜት ነው ማለት ነው?

***ሥርጉት***፦ አዎና፤ ለምሳሌ “ጉንፋን ያዘኝ” ስል፣ “እኔ ምንም ኃላፊነት የለብኝም፤ ሕመሙ መጣብኝ፣ ሕመም ይሰማኛል ማለት አይደለም።”

***ሳሙኤል***፦ እሺ፣ የተለየ ትርጉም ስጭና።

***ሥርጉት***፦ ለኔ፣ ፍቅር ውሳኔ ነው። እንዲህ ባይሆንማ፣ ለምንድነው ክርስቶስ “አዲስ ትእዛዝ” እሰጣችኋለሁ ያለው? ትእዛዝ ሲባል እኮ፣ አውቀን፣ ፈልገን የምናደርገው ነገር ነው። “ፍቅር ይሰማችሁ፣ ሳይሆን፣ የተባለው፣ አፍቅሩ ነው።

***ጥበቡ***፦ በጣም የሚመስጥ ውይይት ይዛችኋል።

***ኀሊና***፦ እኔም አድናቆቴን ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ። እንደ እውነቱ ከሆነ የውይይት ርእሳችሁ እጅግ አስገራሚ ነው።

***ጥበቡ***፦ አንድ ነገር ላንሳ፤ ፍቅር ስሜትም፣ ውሳኔም ነው ብንልስ?

***ሳሙኤል***፦ አስታራቂ ሐሳብ ሊባል ይችል ይሆናል። ነገር ግን የሚበቃ አይመስለኝም።

***ጥበቡ***፦ እንዴት?

***ሳሙኤል***፦ ለሁለቱም ጉዳዮች ማስረጃ ያስፈልጋላ? ለምንድነው ስሜት የሚባለው? ለምንስ ነው ውሳኔ ሊባል የሚችለው?

***ኀሊና***፦ እኔም በዚህ ሐሳብ እስማማለሁ።

***ጥበቡ***፦ በመጀመርያ የፍቅር ዓይነቶችን መመልከት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ለምሳሌ የእናት እና የወላጅ ፍቅር አንድ ገጽታ ነው። ይህ ከተፈጥሮ ጋር በጣም ይያያዛል። የጓደኛ ፍቅር ደግሞ ሌላ ገጽታ ነው። የባልና የሚስት ፍቅር ደግሞ እራሱን የቻለ ሌላ ርእስ ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር ደግሞ የተለየ ቁም ነገር ነው።

***ሳሙኤል***፦ የተለያዩ ነገሮች እየደባለቅን እንዳይሆን።

***ሥርጉት***፦ አልገባኝም።

***ሳሙኤል***፦ በጣም የተለያዮ ነገሮችን ባንድ ላይ “ፍቅር” ካልናቸው ግራ የሚያጋባ ነገር አይሆንም? አሁን ለምሳሌ የሰውን ፍቅርና የአምላክን ፍቅር እንዴት ባንድ ላይ፣ በተመሳሳይ ቃላት ልናስረዳ እንደፍራለን።

***ሥርጉት***፦ የሁሉም ፍቅሮች ምንጭ እግዚአብሔር ስለሆነ የእሱም ፍቅር ቢጠቀስ ችግር የለውም፤ እንዲያውም አስፈላጊ እኮ ነው።

***ኀሊና***፦ የሥርጉት ሐሳብ እዚህ ጋ ተስማምቶኛል። ሁሉንም ፍቅሮች የፈጠረው እርሱ ነው። ***ሳሙኤል***፦ አሁን ለምሳሌ የወንድና የሴት ፍቅር ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር እንዴት ሊገናኝ ይችላል?

***ኀሊና***፦ እርግጥ ነው፣ እግዚአብሔር ጾታ የለውም። ወይንም የጥንት ሕዝቦች፣ ግሪኮችም ወይንም ሮማውያን፣ ባቢሎናውያንም ሆነ የጥንት ግብጻውያን ወንድና ሴት አማልክት ነበሯቸው። እነዚህም አማልክት ሲፋቀሩ ወይም ሲጣሉ ይታያል። የመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ግን ከጾታ ባሻገር ሲሆን፣ ጾታን መልካም አድርጎ ነው የፈጠረው። ከአሪት ዘፍጥረት አንድ እንደምንረዳው ጾታ መለኮታዊ ሆነ ሰይጣናዊ አይደለም።

***ሥርጉት***፦ እንዴ! የእግዚአብሔር ፍቅር ፍጹም፣ ንጹሕ እና ቅዱስ ነው። የሰው ፍቅር ግን በግብዝነት የተሞላ ነው። እንዴት የጾታ ፍቅር መልካም ብቻ ነው ለማለት ይቻላል? ስንት መካካድና ማስመሰል በየዘመኑና በየቦታው ይታይ የለም እንዴ?

***ኀሊና***፦ ከጅምሩ፣ እግዚአብሔር ሲፈጥረው መልካምና ውብ ነበር ማለቴ ነው። አሁን የምትይው ግን ከሰው ትዕቢትና ራስ ወዳድነት ጋር የተያያዘ ነው። አንዴ የተሰበረና፣ ጥገና የሚያስፈልገው ነገር አለ ማለት ነው።

***ጥበቡ***፦ ዞሮ ዞሮ የሰውንና የእግዚአብሔርን ፍቅር ልዩነት ማስተዋል የሚያስፈልግ ይመስለኛል።

***ኀሊና***፦ እኔ እንኳን ከማራራቅ ብናቀራርባቸው የሚሻል ይመስለኛል።

***ጥበቡ***፦ ለምን?

***ኀሊና***፦ እኔ እንጃ፤ እግዚአብሔር እንኳን ፍቅሩን ለመግለጥ በቃሉ የሰጣቸው ምሳሌዎች የሰው ፍቅሮችን ነው። በትንቢተ ሆሴዕ ውስጥ እግዚአብሔር እንደ አባትና እናት (11)፣ እንዲሁም እንደ ፍቅረኛ ተገልጿል (1-3)። ቅርርብ ባይኖራቸው ለምን የእግዚአብሔር ቃል ይህንን እንደ ምሳሌ ያቀርብልናል?

***ጥበቡ***፦ የሰው ፍቅር ምንም አያዋጣም። የእግዚአብሔር ግን ያዋጣል፤ የሰው ፍቅር ያልፋል። የእግዚአብሔር ፍቅር ግን ለዘላላም ይኖራል። የሰውን ፍቅር መጠራጠር አይሻልም?

***ኀሊና***፦ እስቲ ክርስቶስን እንመልከት። አላዛርን ይወደው ስለ ነበር አለቀሰ። ለሚወደው ደቀ መዝሙር ጥልቅ ምሥጢርን ገለጠ። ለኢየሩሳሌም አለቀሰ። ለሰዎች ራራ። ወንጌልን ስናሰላስል የምናየው ክርስቶስ በሰው ልጅ ውስጥ ያሉትን የተፈጥሮ ፍቅሮች እንዳከበረ ነው።

***ጥበቡ***፦ ማንም ሰው ከትዳር ጓደኛና ከወላጅ አስበልጦ እግዚአብሔርን ሊወደው እንደሚገባ ክርስቶስ ተናግሮ የለም እንዴ?

***ኀሊና***፦ እሱ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ምን እንደሆነ ማስታወሱ ነው። የእግዚአብሔር መንግሥት ጉዳይ ከሁሉም ነገሮች እንደሚበልጥ ለማሳየት ተነገር እንጂ አሁን በምትለው መንገድ ልንረዳው አይገባም። ክርስቶስን ለመውደድ የጾታን ፍቅር መጥላት ቢያስፈልግ ኖሮ ክርስቶስ ወደ ቃና ዘገሊላ ለምን ሄደ? ሕፃናት መቀበል ለምን ወደደ? ልጆቻቸው ለታመሙባቸው እናቶች ለምን ራራ? እኔ እንደሚመስለኝ የእናትን ፍቅር፣ የጓደኛን ፍቅር፣ የጾታን ፍቅር የፈጠረውና የሰጠው እግዚብሔር መሆኑን ስናስተውል የሚጣሉ የሚመስሉ ነገሮች የሚስማሙ ይመስለኛል። ለያይተን ስናያቸው ነው የሚጣረሱ የሚመስለን። ይልቁንም የሰው ፍቅሮች አይበቁም ብንል ነው የሚሻለው። አዎን፣ ምን ያክል ውብና አሰደሳች ቢሆኑ እንኳ ከእግዚአብሔር ፍቅር ብቻ የሚመጣውን ሙላት መተካት አይችሉም።

***ጥበቡ***፦ ወደ ብዙ ምርምር እየወሰድሽን ነው።

***ኀሊና***፦ “ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ” ያለ አምላክ “እግዚአብሔርን አምላክን በፍጹም ልብህ” ወደድ ማለት የሰውን እና የአምላክን ፍቅር ማቀራረብ አይደለም እንዴ? እግዚአብሔር በፍጹም ልብ ለመውደድ እንድትችል፣ የትዳር ጓደኛህን፣ የሕይወት ጓደኛህን ወይንም ወላጆችህን በመጠኑ፣ እየቆጠብክ ወደድ አይደለም የተባለው። ታላላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች እኮ ሰውንም፣ ያለ ምንም ማስመሰል፣ በሙሉ ልባቸው ነው የወደዱት። እራሳቸውንም እስከ መስጠት ድረስ።

***ሥርጉት***፦ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክትስ ስለዚህ የሚለው ይኖር ይሆን?

***ኀሊና***፦ በሚገባ፤ በክርስቶስ ፍቅር የተቃጠለው ጳውሎስ እኮ እንዲህ ይላል፦ “ነገር ግን ወንድሜንና ከእኔ ጋር አብሮ ሠራተኛና ወታደር፥ የእናንተ ግን መልእክተኛ የሆነውና የሚያስፈልገኝን የሚያገለግለውን ኤጳፍሮዲጡስን ወደ እናንተ መላክ ፍጹም አስፈላጊ ሆኖ አገኘቼዋለሁ፤ ሁላችሁን ይናፍቃልና፤ እንደ ታመመም ስለ ሰማችሁ ይተክዛል። በእርግጥ በጠና ታሞ ለሞት ተቃርቦ ነበርና፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ማረው፤ እግዚአብሔርም እንዲህ ያደረገው ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ሐዘን በሐዘን ላይ እንዳይደራረብብኝ ለእኔም ደግሞ ነው።” (ፊልጵስዮስ 2፡ 25-27).

ይህ የሚያሳየን ጳውሎስ በሙሉ ልቡ ክርስቶስን መውደዱ፣ አብሮት የሚሠራውን ወዳጁን ከመውደድ አልከለከለውም። የወዳጁ መሞት ምን ያህል ሊያሳዝነው እንደሚችል ገልጿል። ወደ ቆሮንጦስ ሰዎች በላከው በመጀመርያይቱ መልእክት ውስጥ እጅግ የሆነ የፍቅር ውዳሴ ያቀርባል። በዚህም ፍቅር እንደማይቀና፣ እንደማይታበይ፣ እውነትን እንደሚወድ፣ ተስፋ እንደሚያደርግ ሲነግረን እነዚህ ሁሉ ነገሮች የሰው ፍቅሮች እንደሚመለከቱ ግልጽ ነው። ብዙ ችሎታና ተግባር ኖሮኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ መሆኔን ያስረዳኛል።

***ሥርጉት***፦ አሁን ያልሽው በጣም ተስማምቶኛል።

***ጥበቡ***፦ ዓለም የምትድነው ፍቅር እውነተኛ ንግሥት ስትሆነው የምትይ መሰለኝ።

***ኀሊና***፦ እንዴታ! ዓለም የምትድነው በእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ደግሞ ፍቅር ነው!

### ብፁዕ ወቅዱስ ርዕሰ...

ከገፅ 4 የዞረ

ይህንን መንፈሳዊ ልምምድ በሶስት መሰረታዊ መልኮች እንድታዩት አበረታታችኋለሁ። በመጀመሪያ እግአብሔርን ማመስገን ማለትም እግዚአብሄርን ስለሰጠን ስጦታዎች ሁሉ በተለይም ስለሰጠን ሕይወት ከልባችን እናመስግነው። በመቀጠል እግዚአብሔርን መሻት፣ እርሱን የመፈለግ ልባዊ የሆነ መሻትን እና መጠማትን እንዲሰጠን እንለምነው።በመጨረሻም ንስሐ መግባት ማለትም የሕሊና ምርመራ በማድረግ በተለያዩ ጊዜያት የሄድንባቸውን የስህተት መንገዶችንና ውሳኔዎችን በመመልከት ተጸጽተን ወደ አምላካችንና ወደ ወንጌሉ ብርሃን እንመለስ።

### 4. የተስፋ ነጋዲያን ለተልዕኮ

ጉዞአችሁን ሊመራ የሚችል አንድ ተጨማሪ ሀሳብ ቀስቃሽ ምስልን እንዳጋራችሁ ፍቀዱልኝ። በሮም የሚገኘውን የቅዱስ ጴጥሮስን መንበር ለመጎብኘት የሚመጡ ሁሉ በታዋቂው አርክቴክት እና ቀራጺ ጂያን ሎሬንዞ ቤርኒኒ በተገነባው “ኮሎኔድ” የተከበበውን ትልቁን አደባባይ ያቋርጧሉ። ሙሉ “ኮሎኔዱ” ሁለት የተከፈቱ እጆችን ያመለክታል እነርሱም የቤተክርስቲያናችን እና ሁሉንም ልጆቿን ሰብስባ የምትይዝ የእናታችን እጆች ናቸው። በዚህ በሚመጣው የተቀደሰ የተስፋ ዓመት ልክ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትውፊቶች ስለኢዮቤልዩ ዓመት እንደሚያስረዱን ሁላችሁም ይቅር ባይ አምላካችንን እንድትቀርቡት፣ ይቅርታውን እንድትለማመዱ፣ “ለውስጥ እዳዎቻችን” ሁሉ የሚሰጠውን ምህረት እንድትቀበሉ እጋብዛችኋለሁ። በዚህ መልኩ በእግዚአብሔር እቅፍ ውስጥ በመሆን በእርሱ እንደገና በመወለድ፣ ከእርሱ በተቀበላችሁት ፍቅር የተነሳ ጓደኞቻችሁንና የእድሜ እኩዮቻችሁን በፍቅር ስትቀበሉ በእናንተ አቀባበል የተነሳ እግዚአብሔር አብ እንደሚወዳቸው ይገነዘባሉ። እያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ መንፈስ ካደረጋችኋቸው ሰዎችን በፈገግታ ማናገር፣ ሞቅ ባለ የጓደኝነት ስሜት መቀበል፣ ጥሩ ፊት ማሳየት፣ ሌሎችን ለማዳመጥ መዘጋጀት፣ ለሌሎች መልካምን ማድረግ እነኚህን ተግባራት በሚቀበሏቸው ሰዎች ዘንድ የበለጸጉ የተስፋ ዘሮች እንዲዘሩ ያደርጋል እናንተም የማትደክሙ የደስታ ልኡካን ትሆናላችሁ።

ወደፊት ስንቀጥል በጉዞው ከእኛ አስቀድመው የሄዱትንና ግባቸውን በማጠናቀቅ በምስክርነታቸው እንዲህ እያሉ ወደሚያበረታቱን ቅዱሳን በእምነት እንመልከት፡ “መልካሙን ውጊያ ተዋግቻለሁ የሩጫውን ውድድር ጨርሼአለሁ፤ እምነትን ጠብቄአለሁ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ጻድቅ ፈራጅ የሆነ ጌታ በዚያ ቀን ሊሸልመኝ የጽድቅ አክሊል አዘጋጅቶ ይጠብቀኛል፤ደግሞም ለእኔ ብቻ ሳይሆን መገለጡን በፍቅር ለናፈቁት ሁሉ ነው።” (2ኛ ጢሞ 4፡ 7-8) የብዙ ወንዶች እና ሴቶች ቅዱሳን ሕይወት ይደግፈናል ያበረታናል።

በርቱ!ሁላችሁም በልቤ ውስጥ ልዩ ቦታ አላችሁ። የተስፋና የፍቅር መንፈሳዊ ተጓዥነታችሁ እንደጸናችሁ ሁሉ በሕይወት ጉዞአችሁም የእርሷን ምሳሌ በመከተል ተስፋዎቻችሁ ሁሉ እስኪፈጸሙ ድረስ የወደፊቱን በትእግስትና በመተማመን ትጠባበቁ ዘንድ ለቅድስት ድንግል ማርያም አሳልፌ እሰጣችኋለሁ።

*ሮም ቅዱስ ዮሃንስ ቤተክርስቲያን ነሀሴ 23/ 2016 የሰማዕቱ ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቁ መታሰቢያ በዓል*

**“ለጸሎትም በቆማችሁ ጊዜ በሰማያት ያለው አባታችሁ ደግሞ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲላችሁ በማንም ላይ አንዳች ቢኖርባችሁ ይቅር በሉት” (ማር. 11፡25)**

# የክቡር አባ ኒኮሊኖ ዲኦርዮ ዘማህበረ ኮምቦኒ አጭር የሕይወት ታሪክ



**"እኔ እሞታለሁ ሥራዬ ግን አይሞትም" ቅዱስ ዳንኤል ኮምቦኒ**

ክቡር አባ ኒኮሊኖ ዲኦርዮ በጣሊያን ሐገር ቸለንጻ ቫልፎርተረ ተብላ በምትጠራ ቦታ እ.አ.አ ሰኔ 19/1958 ዓ.ም. ተወለዱ። በዚሁ በተወለዱበት መንደር ትምህርታቸው ካጠናቀቁ በኃላ፣ ከልጅነታቸው ጀምሮ ያስቡት፣ ያልሙት የነበረው ሚስዮናዊ ካህን የመሆን ህልም እውን ለማደረግ በጸሎት፣ በአገልግሎት፤ በምክር፤ በመትጋት የኮምቦኒ ዘራዓ-ክህነት በመቀላቀል፤ የፍልስፍና ትምህርታቸው ካጠናቀቁ በኋላ፤ በጣሊያን ግዛት በሚገኝ ቬነጎኖ በሚባለው ቦታ የኮምቦኒ ተመክሮ እ.አ.አ ከ1979 ዓ.ም. - 1981 ዓ.ም. አጠናቆዋል።

የተመክሮ ጉዞአቸው ካጠናቀቁ በኋላ፤ ወላጅ ቤተሰቦቻቸውና ጓደኞቻቸው በተገኙበት፤ ወደ ኋላ ላለመመለስ፤ በሕይወታቸው ክርስቶስን ለመከተል የመጀመርያ ቃለ መሐላቸው እ. አ. አ ሰኔ 6/1981 ዓ.ም. ተቀበሉ።

በመቀጠልም ክቡር አባ ኒኮላ ዲኦርዮ፤ ከመጀመርያ መሐላቸው በኋላ፤ የመጀመርያው ክፍል የነገረ-መለኮት ትምህርታቸው በአሜሪካ - ቺካጎ ጀምረው፤ የሁለተኛው ክፍል የነገረ-መለኮት ትህርታቸው በእንግሊዝ ሀገር - ኤልስተሪ በማጠናቀቅ እ.አ.አ ህዳር 3/1985 ዓ.ም. የመጨረሻ መሐላቸው በመፈጸም እ.አ.አ ሐምሌ 9/1986 ዓ.ም. በተወለዱበት፣ ባደጉበት፣ ፊደልበቆጠሩበት፤ በጣልያን ሀገር በሉቸራ -ትሮያ ሀገረ- ስብከት እጅግ በርካታ ምዕመናን በተገኙበት ማዕረገ ክህነታቸው ተቀበሉ።

በዚሁ ዕለት ሥረዓተ-ቅዳሴ እንደተጠናቀቀ የማህበራቸው የበላይ ኃላፊ ከእንኳን አደረሰዎት መልዕክታቸው በማያያዝ ክቡር አባ ኒኮላ ዲኦርዮ ምድባቸው ለመጀመርያ ጊዜ እዛው በትውልድ ሀገራቸው እንዲያገለግሉ ተመድበው እ.አ.አ ከሐምሌ 1/1986 ዓ.ም. እስከ ሰኔ 30/1993 ዓ.ም. ለሰባት ዓመት ለወዳፊት እንደ እሳቸው በማህበራቸው ገብተው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማገልገል ለሚሹ ወጣቶች ኃላፊ በመሆን አገልግለዋል።

ክቡር አባ ኒኮላ ዲኦርዮ ከልጅነታቸው ጀምሮ በልባቸው ይመላለስ የነበረው በአፍሪካ ለማገልገል ከነበራቸው ጥልቅ ፍላጎት የተነሳ ይህን ሕልም የተረዱት የማህበራቸው የበላይ ኃላፊ ክቡር አባ ኒኮላ ዲኦርዮ እ.አ.አ ሰኔ 1/1993 ዓ.ም. ለመጀመርያ ጊዜ ወደ አፍሪካ ወደ የኢትዮጵያ ተመድበው መጡ።

ክቡር አባ ኒኮላ ዲኦርዮ የአማርኛና የሲዳምኛ ቋንቋ ትምህርታቸው እንዳጠናቀቁ በዚሁ በሀዋሳ ሀገረ ስብከት በተለያዩ ቁምስናዎች ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል።

በቱሎ ቁምስና እ.አ.አ ከሐምሌ 1/1993 - ህዳር 30/1994 ዓ.ም.፤ ፉላሳ ቁምስና እ.አ.አ ከታኅሣሥ 1/1994- መስከረም 30/1999 ዓ.ም. ፤ ጤጥቻ ቁምስና እ.አ.አ ከጥቅምት 01/1999 - ሰኔ 27/2003 ዓ.ም.።

በመህል ለጥቂት ወራት የተሐድሶ ጊዜ እና አጫጭር ትምህርቶች ተምረው እንደገና ለሁለተኛ ጊዜ ክቡር አባ ኒኮሊኖ ዲኦርዮ እ.አ.አ ከሐምሌ 2004 -ነሐሴ 30/2005 ዓ.ም. በጤጥቻ ቁምስና አገልግለዋል።

በመቀጠልም በአዲስ አበባ የማህበራቸው የፋይናስና የንብረት ክፍል የበላይ አለቃ በመሆን እ.አ.አ ከጥቅምት 01/2005 ዓ.ም. - ግቦት 15/2012 ዓ.ም.፤ በጣለያን ሀገር እ.አ.አ ከሐምሌ 01/2012 - ኅዳር 31/2016 ዓ.ም. ለአራት አመት ካገለገሉ በኋላ፤ ለሁለተኛ ዙር እ.አ.አ ከጥር 01/2017 - ግንቦት 31/2020 ዓ.ም. በአዲስ አበባ የማህበራቸው የፋይናስና የንብረት ክፍል የበላይ አለቃ በመሆን አገልግለዋል።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ዓመታት ቁጥሮች ብቻ ሳይሆኑ፤ ክቡር አባ ኒኮላ ዲኦርዮ ለብዙ ሰዎች ተክሊል ያሰሩበት፣ ትምህርተ ክርስቶስ ያስተማሩበት፤ ለበርካታ ወጣቶች የትምህርት ስኬቶቻቸው እውን ለማድርረግ ከጎናቸው የቆሙበት፣ ለበርካታ የተቸገሩት፣ ያዘኑት፣ ያጡት ያዩበት፤ እንዲሁም በሀሳብ ፣በሞራል፣ በምክር፤ የረዱበት ወቅቶች ነበሩ።

ክቡር አባ ኒኮላ ዲኦርዮ እደሚታወቀው ክቡር አባ ጎንጻለስ ኙኘስ ኹዋን አንቶኒዮ የሀዋሳ ሀገረስብከት ሐዋርያዊ አስተዳዳሪ ሆነው ሲሾሙ በማህበረ ኮምቦኒ መልካም ፍቃድ፤ እሳቸው ከነበሩበት የዳዮ ቁምስና ወዳ ሀዋሳ በመዛወር የሐዋርያዊ አስተዳዳሪ እንደራሴ ሆነው እ.አ.አ ከ 2021 - ጥቅምት 2024 ዓ.ም. አገልግለዋል።


ክቡር አባ ኒኮላ ዲኦርዮ የተለመደው የአንድ ወር የዕረፍት ጊዜያቸው በጣልን ሀገር ከወላጆቻቸው፤ ከሚወዳቸው ጓደኞቻቸው፤ አሳልፈው ወደ ሚወዱት፣ ወዳ ህልማቸው ወደሆነችው ወደ ኢትዮጵያ እ.እ.አ ጥቅምት 5/2024 በሰላም አድስ አበባ ከገቡ በኋላ፤ ጥቅምት 6/2024 ባደረባቸው የአጭር ጊዜ ህመም ከዚህ ዓለም ድካም አረፉ።

እግዚአብሔር ነፍሳቸውን በአጸደ ገነት ያኑርልን። አሜን!

ጥቅምት 10/2024 ዓ.ም. ፤ ሀዋሳ

# የወንጌል አርበኛ ካቴኪስት ገ/ኢየሱስ ዳለቾ የሕይወት ታሪክ በአጭሩ

1921 ዓ.ም - 2016 ዓ.ም



***"ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፤ ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም፤ ከሁላችሁ ይልቅ ግን ደከምሁ÷ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም።"***

**1ቆሮ. 15÷10**

ካቴኪስት ገ/ኢየሱስ ከአባታቸው ከአቶ ደላቾ በዶሬና ከእናታቸው ከወ/ሮ ሎዳሜ ለፌቦ በከምባታ አውራጃ በአንጋጫ ወረዳ ልዩ ስሙ ጎሞራ ገዋዳ ቀበሌ በ1921 ዓ.ም. ተወለዱ።

ካቴኪስት ገ/ኢየሱስ ወላጆቻቸው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ስለነበሩ በልጅነታቸውም በተዋሕዶ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሥር ስላደጉ ከ1933 ዓ.ም እስከ 1938 ዓ.ም መሠረተ ትምህርትን፣ የግዕዝ ቋንቋ እና ዜማ በአንጋጫ ከተማ በሚገኘው ቅድስት ማርያም ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥር ሆነው ተምረው ስከ ድቁና አገልግሎት ደርሰዋል።

የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሚሲዮናውያን ወንጌልን በአካባቢው ሲመጡ በአካባቢው መግባቢያ ቋንቋዎች በአማርኛና በከምባትኛ ተርጉመው ሲያስትምሩ በማየት በመደነቅ የካቶሊክ እምነት ተከታይ ለመሆን ተሳቡ።

ከ1941 ዓ.ም. ጀምረው በካቶሊክ ቤተክርስቲያን መሰረረታዊ ትምህርት ተምረው በዋሠራ ቅድስት ቴሬዛ ቁምስና በሚገኙ 39 መንደራት ውስጥ እየዞሩ በማስተማር የወንጌል ሐዋርያነት አንድ ብለው ጀመሩ። ካቴኪስት ገ/ኢየሱስ በ27 ዓመታቸው በ1948 ዓ.ም የዶዮ ገና ኮምቦኒ ትምህርት ቤት መሥራች ከነበሩት ሲስቴር ማርገሪታ ድንቅሰው ጋር በመመካከር ወደ ገዳም ለመግባት ፍላጎት እንዳላቸው ሲገልጹ በኮምቦኒ ማህበር አለቆች አማካይነት ተመርጠው ለክህነት የጥሪ ትምህርት ለመከታተል ወደ አሥመራ ተላኩ። ክህነት ጥሪያቸው አለመሆኑን በመገንዘብ ወደ ትውልድ ቦታቸው ቅድስት ቴሬዛ ቁምስና ዋሠራ ተመልሰው የካቴክስትነትን ኮርስ በአሁኑ ሲዳማ ክልል ሐዋሳ ሀገረስብከት በሚገኘው በዶንጎራ የሐዋርያዊ አገልግሎት ማሰልጠኛና በተለያዩ የካቶሊክ ሐዋርያዊ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የስብከተ ወንጌልን ሥልጠና በመከታተልም ካቴኪዝም ወይም ትምህርተ ክርስቶስ አስተማሪ ደቀ መዝሙር ሆነው ተሰየሙ ።

## የካቴኪስት ገብረ ኢየሱሰ የወንጌል ተልዕኮ በጠምባሮ

በ1951 ዓ.ም የከምባታና ሀድያ አውራጃ ጳጳስ የነበሩት ሞንስኞር አቡነ ኡርባኖስ የወንጌልን ተልዕኮ ለመፈጸም ከፈረንሳይ ሀገር የመጡትን የማኅበረ ካፑቺን ሚሲዮናዊ ክቡር አባ ማርሻልን ወደ ጠምባሮ እንዲሄዱ ሲመደቡ አባ ማርሻል ለሐዋሪያዊ ሥራ ጠምባሮ ለመሄድ ባህሉንና ቋንቋውን የሚችል ሰው ሲፈለግ ገብረየሱስ ይችላል ተብሎ ስለተነገረ ካቴኪስት ለዚህ አገልግሎት ታጩ። በ1951 ዓ/ም ከፈረንሳያዊ ካህን አባ ማርሻል ጋር ሆነው ባለቤታቸውንና የመጀመሪያ ልጃቸውን ይዘው ጠምባሮ ልዩ ስሙ ኮጳቴ በሚትባል መንደር ሐዋርያዊ አገልግሎታቸውን ማበርከት ጀመሩ። በጠምባሮ አካባቢ የክርስትና እምነትን በማስፋፋት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ የእምነት አባት ነበሩ። የጠምባሮ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ካቴኪስት ሆነው ወንጌልን እየሰበኩ ትምህርተ ክርስቶስንም ያስተምሩ ነበር። በጸሎትና በትምህርትም መካከል የራሳችው የሆኑትን ባህላዊ ዜማዎችን ያዜሙ ነበር። በተለይም በለቅሶ ጊዜ ከሚያዜሙ ዜማዎች አንዳንዱ (ኦነት ዮባአ) ለቅሶ የለም፣ ተሶ ዮኔ (ተስፋ አለን) የሚሉትን መጥቀስ ይቻላል። በእምነት አስተምህሮ ጎን ለጎን በጠምባሮ ኮጳቴ ተብሎ በሚጠረው የካቶሊክ ትምህርት ቤት ከመጀመሪያዎቹ የቋንቋ አስተማሪዎች አንዱ ነበሩ።

ካቴኪስት ገብረኢየሱስ በጠምባሮ ምድር በእግራቸው እየተዛዋወሩ ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ የካቶሊክ እምነትን ካስፋፉዋቸው መንደራት መካከል ዱርጊ፣ ኮጳቴ፣ጌዴራ፣ዘምባራ፣ ሞግሳ፣ጎፎረ፣ ወለቃ፣ ግዶሌ፣ ገርማሞ ወዘተ መጥቀስ ይቻላል። ሁሉም የጠምባሮ ምእመናን ካቴኪስት ገብረኢየሱስን በወንጌል አግልግሎታቸው እስከዛሬም ያስታውሳሉ።

ካቴኪስት ገ/ኢየሱስ ዳለቾ ከቤተክርስቲያን አገልግሎት በተጨማሪ ማኅበራዊ ልማት ዘርፍም በጠምባሮ በቀድሞ ስሙ አሞሸለቆ ወረዳ ሙዱላ ማዘጋጃ ቤትም በጸሓፊነትና በውሃ ልማት ቢሮ ሃላፊነት በልማት ሥራዎች የካቶሊክ ቤተክርስቲያንን በመወከል በተጠሪነት አገልግለዋል።

የካቴኪስት ገብረኢየሱስ ህልምና ራዕይ የነበረው የወንጌልን ተልእኮ ከጠምባሮ አልፎ የኦሞ ወንዝን ተሻግሮ ወደ ደውሮ ኮንታ ማድረስ በሚል ይዘውት የነበረው ሀሳብና ግምት በአባ ራፌሎና በአባ ሬንዞ ተነሳሽነት

ወደ ገፅ 11 ዞሯል

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የሴቶችና ቤተሰብ ጉዳይ ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**"በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ እንጂ በምንም ዓይነት ነገር አትጨነቁ" (ፊል. 4፡6)**

# የጸሎት ሐዋርያነት



## ህዳር

**ልጃቸውን ላጡ ሁሉ**

ወንድ ወይም ሴት ልጃቸውን በማጣታው ምክንያት ሐዘን ላይ ላሉ ወላጆች በሙሉ ከህብረተሰቡ ድጋፍን እንዲያገኙ እንዲሁም ከመንፈስ ቅዱስ ሰላም እና መፅናናትን እንዲቀበሉ እንፀልይ።

## November

***For anyone who has lost a child***

**We pray that all parents who mourn the loss of a son or daughter find support in their community and receive peace and consolation from the Holy Spirit.**

## የማቅረቢያ ጸሎት

*ቅዱስ አባት ሆይ ሁሌም ከእኔ ጋር እንደምትሆን አምናለሁ ፤ ልቤን በየቀኑ በቅዱስ ቁርባን ራሱን በሚሰጠን በልጅህ በኢየሱስ ልብ ውስጥ አኖራለሁ። ቅዱስ መንፈስህ እኔን ወዳጅህ እና ሐዋርያህ ያድርገኝ ለአገልግሎትም ዝግጁ እና ቀናኢ ያድርገኝ። ደስታዬን፣ ስቃዬን፣ ተስፋዬን፣ ሥራዬን፣ ሁሉ ነገሬን በዓለም ካሉት የፀሎት ሐዋርያቶች ጋር በአንተ እጅ አኖራለሁ። ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ቀኔን ለቤተክርስቲያን ተልዕኮ አቀርባለሁ! በር.ሊ.ጳ የፀሎት ሐሳብም እፀልያለሁ!*

# በጋልዬ ሮግዳ ሃና ማርያም ካቶሊክ ትምህርት ቤት በሕፃናት እንክብካቤ እና ጥበቃ ዙሪያ ለሠራተኞች ሥልጠና ተሰጠ

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን በእምድብር ሀገረስብከት ጠቅላይ ጽ/ቤት በሐዋርያዊ ዘርፍ ውስጥ ከሚገኘው ጥበቃ እና እንክብካቤ ክፍል አዘጋጅነት በሕፃናት እንክብካቤ እና ጥበቃ የትምህርት ቤቶች ኃላፊነትን በተመለከተ በእምድብር ሀገረስብከት ሥር የሚገኘው የጋልዬ ሮግዳ እና መካኖ ካቶሊክ ትምህርት ቤት ሠራተኞች የአንድ ቀን ሥልጠና ተሰጠ።

እንደ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ እና የወንጌል እሴቶች መሠረት ሕፃናት ልዩ ትኩረትና እንክብካቤ የሚያሻቸው እንደሆነ የሚታወቅ እውነታ በመሆኑ ይህ ሥልጠና በካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አዘጋጅነት የተዘጋጀ ቢሆንም እምነት ተኮር ብቻ የሆነ ጉዳይ አይደለም፤ ኃላፊነቱም የእያንዳንዳችን ነው።

ሕፃናት እንክብካቤ የሚያሻቸው በመሆናቸው በሁሉም ዘርፍ ልንንከባከባቸው እና ከሚደርስባቸው አካላዊም ሆነ ስነልቦናዊ ጉዳት ልንጠብቃቸው እና ማንኛውንም ዓይነት ጥቃት ያደረሰባቸውን አካል ለሕግ በማቅረብ ለእነዚህ ሕፃናት ድምጽ መሆን የሁላችንም ግዴታ ነው።

ዛሬ ላይ በእጃችን ላይ ያሉ ሕፃናት ከጤና፣ አካላዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ትምህርታዊ፣ መንፈሳዊ እንዲሁም በሌሎች ዘርፎች እንክብካቤ ቢደረግላቸው ነገ ላይ ከራሳቸውም አልፎ ለሌሎችም የሚደርሱ እና ለታላላቅ ደረጃ የሚበቁ የማኅበረሰባችን አካል ማበርከት ይቻላል። ነገር ግን ዛሬ ላይ በቸልተኝነት እንዲሁም ባለማወቅ ሕፃናት ላይ ወሲባዊ፣ ስነልቦናዊ እና አካላዊ የጉልበት ብዝበዛ በማድረግ ሕፃናትን ለአደጋ በማጋለጥ ሕፃናት በወደፊት ሕይወታቸው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዲደርሱ ኃላፊነታችንን ባለመወጣት ለተለያዩ ጉዳቶች እየተዳረጉ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

ሕፃናት በራሳቸው ጊዜ ለራሳቸው መቆም የማይችሉ ስለሆኑ ድምጽ ልንሆናቸው ይገባናል። በተለይም በትምህርት ቤት ከሕፃናት ጋር የምንሠራ መምህራን እና ሌሎች ሠራተኞች ጉዳዩ የጋራ የተቀናጀ ሥራ የሚጠይቅ በመሆኑ ነገ የተሻለ ሀገር ለመፍጠር እንዲቻል የሚጠበቅብን ሁሉ መወጣት እንዳለብን ከተሳታፊዎችም ተገልጿል።

ይህን ሥልጠና የሰጡት የእምድብር ሀገረስብከት ጠቅላይ ጽ/ቤት አስተዳደር እና የሕፃናት ጥበቃና እንክብካቤ ተጠሪ የሆኑት አቶ ቁምላቸው ወ/ገብርኤል ሲሆኑ በዓለቱም ከጠቅላይ ፅ/ቤቱ የጤና እና የትምህርት ክፍል ተወካዮች ስልጠናው ላይ ተሳትፈዋል።

*ምንጭ፥ የእምድብር ሀገረስብከት ማኅበራዊ ተግባቦት*

**የወንጌል አርበኛ...**

ከገፅ 10 የዞረ

እንዲሁም በሌሎችም ሚሲዮናዊያን አማካይነት ዛሬ የካቶሊክ በተክርስቲያን በደውሮ ኮንታ ተስፋፍቶ ማየት የሚለው ራዕይ ተፈጽሞ አይተዋል።

**የወንጌል አገልግሎት በቅድስት ቴሬዛ ቁምስና በዋሠራና**

በገዋዳ ካቴኪስት ገብረኢየሱስ በ1960 ዓ ም ከጠምባሮ ከተመለሱ በኋላም ከጎሞረ ገዋዳ ቀበሌ ከገዋዳ መንደር ወደ ቅድስት ቴሬዛ ቁምስና ዋሠራ የ16 ኪ.ሜ. መንገድ በሳምንት 2 ጊዜ እየተመላለሱና ከዚያም አልፈው ከመኖሪያ ቤታችው 30 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ የሚገኙ መንደራትን ተመድበው እየዞሩ በሳምንቱ ቀናት ወንጌልን ያስተምሩ ነበር።

ካቴኪስት ገብረኢየሱስ በተመደቡበቸው መንደራት የተስፋ ማህበርተኞችን ቡድን በማቋቋም የተስፋ ሥራ ሲሠሩና ሲያሠሩ ተሶ ዮኔ(ተስፋ አለን) የሚለውን ባህላዊ ዜማና ሌሎችንም ተመሳሳይ ዜማዎችን በመምራትና በማዜም ምዕመናንን እያበረታቱ ይሠሩም ያሠሩም ነበር።

ካቴኪስት ገብረኢየሱስ ካቴኪስት ገ/ኢየሱስ ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳያ የተፈጠረ ስለሆነ ሁሉም እኩል ነው በማለት ለፍትህና ለእውነት የቆሙ አባት ነበሩ። ቅን፣ በሐሰት የማይፈርዱ፣ የተጣሉትን የሚያስታርቁ፣ የታመሙትንና የታሰሩትን የሚጠይቁ፣ የሚያስታርቁ፣ ህጻናትንና ሴቶችን በልዩ አክብሮት ፍቅር የሚያዩና ካላቸው ለተቸገሩ የሚያካፍሉ ነበሩ። በገቡበት ቤት ሁሉ የእምነት ልዩነት ሳያደርጉ ጸሎት ያደርጋሉ፣ ቃለ እግዚአብሔርን ያሰማሉ እና የጸሎት ሕይወት እንዲኖሩም ይመክሩ ነበር። በካቴኪስትነት በወር ከሚከፈልላቸው 40 ብር አሥሩን ብር ለሌላ ረዳት ካቴኪስት እየከፈሉ ተተኪ ሰባኪ የማፍራት ሥራ ሠርተዋል።

ካቴኪስት ገ/ኢየሱስ በ1950 ዓ.ም ከወ/ሪት ፍቅረ ማርያም ጋዶሬ ጋር በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ሕግ፣ ደንብና ሥርዓት መሠረት በዋሠራ ቅድስት ቴሬዛ ቁምስና ምሥጢረ ተክሊላቸውን/ ቃልኪዳናቸውን ፈጸሙ። ከትዳር አጋራቸው ጋር በመሆን አራት ወንድ ልጆችና ሁለት ሴት ልጆችን ከማፍራታቸውም በላይ የልጅ ልጆችንና የልጅ ልጅ ልጆችን ወግ ማዕረግ የበቁ አባት ነበሩ። የወለዱአቸውን ልጆች ሁሉንም ከማስተማራቸውም በላይ ሁሉንም ለወግ ማዕረግ አብቅተዋል።

ለካቴኪስት ገብረኢየሱሰ ዳለቾ የሐዋርያዊ ሥራቸው ስኬትና፣ ልጆቻቸውን የማስተማርና በሥነ ምግባር የማሳደግ ዋና ምስጢሩ ከእግዚአብሔር በታች የባለቤታቸው የወይዘሮ ፍቅረማርያም ጋዶሬ ነበር። ወይዘሮ ፍቅረማርያም ጋዶሬ በ1928 ዓም በዱራሜ በዘና ቤናራ ልዩ ስሙ ምሽከዳ ተወለዱ። በ1950ዓም በተወለዱ በ22 ዓመታቸው ከካቴክስት ገብረኢየሱሰ ጋር ቃል ኪዳን መሠረቱ። ወይዘሮ የፍቅረ ማርያም ጋዶሬ ለልጆችዋ መንፈሳዊ ሕይወት፣ ትምህርትና ለባለቤትዋ ሐዋርያዊ ሥራ በፍጹም ቀኝ እጅ ነበሩ። ወይዘሮ ፍቅረማርያም ጋዶሬ ከካቴኪስት ገብረኢየሱሰ ቀደም ብለው ማለትም ሚያዚያ 15 ቀን 2015 ዓ/ም በክርስቶስ አርፈዋል።

ካቴኪስት ገ/ኢየሱስ መጀመሪያ ተመኝተው ሳይሳካላቸው የቀረውን የክህነት አገልግሎት በእግዚአብሔር ፈቃድ በመጨረሻ ልጃቸው እውን ሆኗል። ካቴኪስት ገ/ኢየሱስ ያስተማሯቸውና ለቃልኪዳን የበቁ ብዙ ቤተሰቦች ምስክሮች ናቸው። እንዲሁም እሳቸው የመሠረቱት የተስፋ ማህበር አባላት በዋሰራ፣ በጠምባሮ፣ በአብዮሶና በገዋዳ ዛሬም ህያው ምስክሮች ናቸው። የሁሉ አፍቃሪነታቸው ፣ አጫዋቺነታቸው፣ ቅንነታቸው ታሪካቸው ሁሌም ይኖራል። ሕይወታቸውም ሆነ ሐዋርያዊ ሥራ ትውስታቸው ሁሌም ሕያው ነው።

በስተመጨረሻም እድሜያቸው ከመግፋቱም በተጨማሪ በጤና እክልም ምክንያት ለቤታቸው ቅርብ በሚገኘው ቅዱስ እስጢፋኖስ ሐዋርያዊ ዞን ሥር በካቴክስትነት እያገለገሉ ቆይተዋል። በተለያዩ ጊዜያት በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ምስጢራትን ከተቀበሉ በኋላ በመጋቢት 11 ቀን 2016 ዓም በተወለዱ 95 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ድካም በክርስቶስ አርፈዋል።

"ጌታ ሆይ ለሙታን የዘላለምን ዕረፍት ስጣቸው፤ ብርሃንህንም አብራላቸው፤ በሰላም አሳርፋቸው። አሜን!!

*እግዚአብሐር በመንግሥቱ ይቀበላቸው ለቤተሰባቸውና ለሰበካቸው መጽናናትን ይስጥልን*

**ይበልጥ ...**

ከገፅ 6 የዞረ

## 4, እርስበርሳችን ይበልጥ መዋደድ

እንደ ወደድኋችሁ ...እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ። እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ እንዳለው ጌታችን ኢየሱስ፡ (ዮሐ. 13፡34) ሰዎችን ሁሉ ከአምናው ይልቅ በመውደድ ፈጣሪያችንን እንደምንወድ እንመስክር። ስንዋደድ ለመኖር ያለን ፍላጎት ይጨምራል፤ ተስፋችን ይለመልማል። በተቃራኒው ደግሞ ኑሮአችን ፍቅር የሌለበት ከሆነ ዓመቱ አዲስ ዓመት ቢሆን እንኳ ሕይወት ትርጉም አልባ ትሆናለች። ስለዚህ የፍቅር ሕይወት ለመኖር እንችል ዘንድ ሰውን በሰውነቱ እንውደድ፤ ከአምናው ይበልጥ በዚህ ዓመት ከዘረኝነትና ከጎጠኝነት አመለካከት በመውጣት እርስበርሳችን ይበልጥ እንዋደድ። ከአምላካችን በተቀበልነው አዲስ ዓመት ‹እኔ› ከሚለው መንፈስ ወጥተን ‹እኛ› ወደሚለው መንፈስ በመግባት ከአምናው ይልቅ ዘንድሮ እርስበርሳችን ይበልጥ በመዋደድ የወደደንን አምላክ እንውደድ።

የሰማይና የምድር ጌታ፡ የዓመታትና የዘመናት ንጉስ የሆነው አምላካችን፡ በሰጠን አዲስ ዓመት ከእርሱ ጋር ያለን ወዳጅነት ይበልጥ በማጠንከርና የአንድ አባት ልጆች መሆናችንን ይበልጥ ለመገንዘብ እርሱን ይበልጥ በማወቅ፡ ትእዛዛቱን በመጠበቅና እርስበርሳችን ይበልጥ በመዋደድ ፍቅራችንን እናድሰው፣ ዓመቱን የ‹ይበልጥ› ዓመት እናድርገው። ከሁሉም የሚበልጠው ፍቅር ነውና።

**ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የሕፃናት እንክብካቤ እና ጥበቃ ቢሮ ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው**

**‹‹የምትወዱኝ ከሆነ ትእዛዜን ትጠብቃላችሁ እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል›› (ዮሐ. 14፡15)**

# የካቶሊክ ማህበራዊ አስተምህሮ

## የማኅበራዊ ፍትህ እና ሥነ ምግባራዊ ሥነ-መለኮት



የካቶሊክ ማህበራዊ አስተምህሮ በዘመናዊው ማህበረሰብ ፈተናዎች መካከል ፍትሃዊ ማህበረሰብን ለመገንባት እና የቅድስና ሕይወትን ለመኖር የጥበብ ሀብት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ እና በቤተክርስቲያን ትውፊት ላይ የተመሰረተ ይህ አስተምህሮ በቁልፍ መርሆች የተገነባ ነው።

ዋና ዓላማው ከማኅበራዊ ፍትህ ጉዳዮች በስተጀርባ የሥነ-መለኮታዊ እና ሥነ ምግባራዊ አስተሳሰብ ላይ አፅንዖት በመስጠት የዚህን ዘመን የሰውን ልጅ አኗኗርና እግዚአብሔር ከሰው ልጅ የሚጠብቀውን ነገር ለማመዛዘን፤ ለማየትና ትኩረት ለመስጠት ነው። ይህ ማህበራዊ አስተምህሮ እጅግ ጠቃሚና በምድር ላይ ትርጉም ያለውን ለውጥ ለማምጣት አቅም ያለው ሆኖ ሳለ በቤተክርስቲያን ውስጥና በሌሎችም በቤተክርስቲያን ጥላ ሥር ባሉ ተቋሞች ማለትም እንደ ትምህርት ቤት፤የጤና ተቋማትና ሌሎችም ውስጥ መታየት በሚገባው ልክ እየታየ አይደለም፤ በዓለም ዙሪያ ያሉ በርካታ የማህበራዊ ተቋማት ከዚህ አስተምህሮ ላይ እየቀነጨቡ በመውሰድ የራሳቸውን ድርጅታዊ ዓላማዎችን ሲያሳኩ ይስተዋላል። ነገር የጉዳዩ ባለቤቶችጋ እምብዛምም ሲስተጋባና ሲተገበር አይታይም፤ ስለዚህ የዚህች አጭር ጽሁፍ ዓላማ በቤተክርስቲያንና በእርሷ ጥላ ሥር ያሉ ተቋሞች ሁሉ ቢቻል ይህንን አስተምህሮ የሥራቸው አካል ቢያደርጉና ቢተግብሩ በእርግጠኝነት ትርጉም ያለው የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ብዬ አምናለሁ። እዚህ ላይ እኔ የሞከርኩት ነገር አዲስ ሃሳብ ለማመንጨት ሳይሆን ይህንን ታላቅ አስተምህሮ በይበልጥ ለማጎልበትና በሃሳብ እየተንሸራሸረ ለብዙዎች እንዲደርስና የተሻለ ለውጥ ለማምጣት በጋራ እንድንሠራ ለማሳሰብ ነው።

የካቶሊክ ማህበራዊ አስተምህሮ ዋና ዋና መርሆች ከዝርዝር ማብራሪያዎች እና ተዛማጅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች ጋር ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን።

### 1. የሰው ልጅ ሕይወት እና ክብር

ይህ መርህ የእያንዳንዱን ሰው ሕይወት ከፅንስ እስከ ተፈጥሯዊ ሞት ድረስ ያለውን የተፈጥሮ ክብር እና ቅድስና ያጎላል። እያንዳንዱ ሰው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረ በመሆኑ ክብርና ጥበቃ ይገባዋል።

የሰው ልጅ ክብር በካቶሊክ ማህበራዊ አስተምህሮ ውስጥ መሰረታዊ መርህ ሲሆን ሰው ሁሉ በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ በመፈጠሩ በተፈጥሮ ዋጋና ክብር እንዳለው ይናገራል። *ዘፍጥረት 1፡26-27* ይህ ክብር ውስጣዊ እና የማይደፈር ክብር መሆኑን ያረጋግጣል፤ ይህም ማለት ለሰውነታችን አስፈላጊ ከሆኑት ዋና ዋና ነገሮች አንዱ እርስ በርስ መከባበር ነውና ምንም አይነት ሁኔታ እና ድርጊት ምንም ይሁን ምን ይህ ተፈጥሮአዊ የሆነው ነገር ሲነካበት የሰው ለጅ በሙሉ ልቡ ይሰበራል፤ ነፍሱ ያዝናል፤ ሥጋው ይታመማል። ሰብአዊ ክብሩ የተነካበት የተዋረደ ሰው ምግብ፤ መጠለያና ልብስ አጥተው ከሚንከራተቱ ወይም ደግሞ በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ አደጋ ከተፈናቀሉ ሰዎች በበለጠ አእምሮው ይጎዳል፤ ስብዕናው ይነካል፤፡

- "እግዚአብሔርም የሰውን ልጅ በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔርም መልክ ፈጠራቸው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።" *ዘፍጥረት 1፡27*
- "በማኅፀን ሳልሠራህ አውቄሃለሁ፥ ሳትወለድም ለይቼሃለሁ፥ ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌ ሾምሁህ።" *ኤርምያስ 1፡5*

ንጉሡም መልሶ "እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼና እህቶቼ ለአንዱ ያደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት አላቸው።" *ማቴዎስ 25:40*

በዚህ መርህ እያንዳንዱ ሰው ክብር እና ጥበቃ እንደሚያስፈልገውና እነዚህን ጉዳዮች እንደ ሰው ሙሉ በሙሉ የማሳደግ እድል ይገባዋል የሚለውን ሃሳብ የካቶሊክ ማህበራዊ አስተምህሮ ይደግፋል; እንዲስፋፋም ይጥራል። የእያንዳንዱ ግለሰብ ልዩ ዋጋ እውቅና እንዲሰጠው ይጠይቃል እናም የሰው ሕይወት ከተፀነሰበት እስከ ተፈጥሯዊ ሞት ድረስ የተቀደሰ መሆኑን ያጎላል. ይህ ውስጣዊ ክብር ለሰብአዊ መብቶች መሰረት ከመሆኑም ባሻገር ለማህበራዊ ፍትህም ዋነኛ እና ማዕከላዊ ጉዳይ ነው። የሰው ልጅ ክብር በተነካበት/በተዋረደበት ቦታ ሁሉ ስለማህበራዊ ፍትህ ማውራት ጨርሶ አይታሰብም።

**የዚህ መርህ አስፈላጊነት፡ -**

- **የሰብአዊ መብቶች መሠረት በመሆኑ፡** የሰው ልጅ ክብር ለሰብአዊ መብቶች የማዕዘን ድንጋይ በመሆኑ ሁሉም የሰው ልጆች መሰረታዊ ፍላጎቶቻቸው ተሟልተው እና ከጭቆናና ከግፍ ተላቀው መኖር እንዳለባቸው በአጽንኦት ያስተምራል።
- **ማህበራዊ ፍትህን ያበረታታል፡** የእያንዳንዱን ሰው የተፈጥሮ እሴት በመገንዘብ፣ ይህ መርህ ድህነትን፣ እፍታዊነትን እና አድልዎን ለመዋጋት ጥረቶችን ያነሳሳል። ግለሰቦች ሙሉ አቅማቸውን እንዲያሳኩ የሚያስችሉ ማህበራዊ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ይጠይቃል።
- **የስነምግባር ማዕቀፍ ነው፡ -** ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ስርዓቶችን ለመገምገም የስነ-ምግባር ማዕቀፍ ሆኖ ይቀርባል። ፖሊሲዎች እና ድርጊቶች የሚዳኙት የእያንዳንዱን ሰው ሰብአዊ ክብር በሚደግፉበት እና በሚያስተዋውቁበት ሁኔታ ላይ ነው። ያለ ሰው ልጅ ሰብአዊ ክብር ማንኛውም ፖሊሲና ተግባር ትርጉም የለውም። የሰው ልጅ ሰብአዊ መብቱን ወደ ጎን የጣለ ማንኛውም የፖለቲካዊ፤ የኢኮኖሚያዊ እና የማህበራዊ አስተሳሰብም ሆነ አስተምህሮ የሜዳ ላይ ጨኸት ሆኖ ይቀራል።
- **የማህበረሰብ እና የአብሮነት መሰረት ነው፡** የእያንዳንዱን ሰው ክብር እውቅና መስጠት የማህበረሰብ እና የአብሮነት ስሜትን ያሳድጋል። ሌሎችን እንደ ወንድም እና እህት እንድንመለከት ያበረታታናል፣ ፍቅር እና ርህራሄ እንድንጨምር ያግዘናል።
- **የሞራል ውሳኔ አሰጣጥን ይመራል፡** - ይህ መርህ ሌሎችን በአክብሮት እንድናይ እና ድርጊታችን በደህንነታቸው ላይ የሚያሳድረውን ተጽዕኖ እንድንገነዘብ በማሳሰብ ሥነ ምግባራዊ ውሳኔዎችን እንድንሰጥ ያግዘናል። የማንም በግለሰብም ሆነ በቡድን የሚወሰን ውሳኔ በመጀመሪያ የሰውን ልጅ ክብር የሚጋፋ መሆን የለበትም።

### 2. ለቤተሰብ፣ ለማህበረሰብ እና ለተሳትፎ ጥሪ

ቤተሰብ መሠረታዊ የሆነ ማህበራዊ ተቋም ሲሆን በማህበረሰብ ሕይወት ውስጥ ደግሞ ተሳትፎ እጅግ አስፈላጊ ነው። የሰው ልጅ ደግሞ ማህበራዊ ፍጡር እንደመሆኑ መጠን በአብሮነት መኖር አማራጭ የሌለው ባህሪው ነው።

የሰው ልጅ የተቀደሰ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊም ነው። ቤተሰብ መደገፍ እና መጠናከር ያለበት ማዕከላዊ የሆነ ማህበራዊ ተቋም ነው.። ሰዎች በህብረተሰብ ውስጥ የመሳተፍ መብትም ግዴታም አለባቸው:

- እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ "ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።" *ዘፍጥረት 2፡18*
- "በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን፥ የብልቶቹም ሁሉ ሥራ አንድ እንዳይደለ፥ እንዲሁ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን፥ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች ነን።" *ሮሜ 12፡4-5*

"እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም፤ የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።" *ዘፍጥረት 1፤28*

ይህ ክፍል በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን የእያንዳንዱን ሰው ውስጣዊ ክብር ይመሰርታል፤ ያጎላል፤ ያሳድጋል። የሰው ልጅ እርስ በርስ እንዲከባበር፤ እንዲፋቀርና ምድርና ሞላዋን እንድንከባከብ ከእግዚአብሔር ኃላፊነት ተስጥቶት ተፈጠረ እንጂ እርስ በርስ ጠላትነት እንዲፈጥር፤ እንዲጠፋፋና ምንድርንም እንዲያጠፋ አልነበረም። ስለዚህ ይህንን አውቀን ለሰው ልጅ የሚገባውን ክብርና ፍቅር እንስጥ፤ ሌሎች ፍጥረታትንም እንጠብቅ፤ እንንከባከብ።

"የጣቶችህን ሥራ ሰማዮችን ባየሁ ጊዜ፥ ጨረቃንና ከዋክብትን አንተ የሠራሃቸውን፥ ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ትጐበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው? ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው፤ በክብርና በምስጋና ዘውድ ከለልኸው። በእጆችህም ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው፤ ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት።" *መዝ 8፤3-5*

ወንድሞቼ ሆይ፥ በክብር ጌታ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን እምነት ለሰው ፊት በማድላት አትያዙ። የወርቅ ቀለበት ያደረገና የጌጥ ልብስ የለበሰ ሰው ወደ ጉባኤአችሁ ቢገባ፥ እድፍ ልብስም የለበሰ ድሀ ሰው ደግሞ ቢገባ፥ የጌጥ ልብስም የለበሰውን ተመልክታችሁ፦ አንተስ በዚህ በመልካም ስፍራ ተቀመጥ ብትሉት፥ ድሀውንም፦ አንተስ ወደዚያ ቁም ወይም ከእግሬ መረገጫ በታች ተቀመጥ ብትሉት፥ ራሳችሁን መለያየታችሁ አይደለምን? ክፉ አሳብ ያላቸውም ዳኞች መሆናችሁ አይደለምን? የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ስሙ፤ እግዚአብሔር በእምነት ባለ ጠጎች እንዲሆኑ ለሚወዱትም ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም ድሆች አልመረጠምን?

*ያዕ 2፡1-5*

ይህ ክፍል አድሎአዊነትን ያወግዛል እናም ሁሉንም ግለሰቦች በተፈጥሮ ክብራቸውን በመገንዘብ በእኩልነት እንዲታዩ ይጠይቃል። ሰውን በድህነቱ፤ በሃብታምነቱ፤ በዘሩ፤ በጎሳው፤ በቋንቋው፤ በሃይማኖቱ፤ በፖለቲካ አመለካከቱ፤ምክንያት ለይቶ ማግለል፤ መጥቀም ወይም መጉዳት በዚህ አስተምህሮ በፍጹም የተከለከለ መሆኑን በግልጽ ያሳየናል። በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንደሚያሳዩን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅ በኤዴን ገነት ውስጥ በሠይጣን ምክንያት ያጣውን ክብር ለመመለስ ከሰማይ ከአባቱ ዘንድ የመጣ እንደመሆኑ መጠን በተለይም ከድሆችና ከተገለሉ ሰዎች ጋር ባደረገው ግንኙነት የፈጸማቸው ድርጊቶችና ያስተማራቸው ትምህርቶች የክርስቶስን ሃሳብ ጎላ አድርገው ያሳያሉ። እነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ ድሆችን፣ የተገለሉትን እና በማህበራዊ ደረጃ ዝቅ ያሉትን ከፍ ከፍ ለማድረግ ያለውን ቁርጠኝነት ያሳያሉ፣ በዚህም የእያንዳንዱን ሰው ተፈጥሯዊ ክብር ያረጋግጣሉ።

"አይሁዳዊ ወይም አሕዛብ የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።" *ገላ 3፡28*

ይህኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የማህበራዊ እና የባህል ልዩነት ሳይለይ የሁሉንም ሰዎች እኩል ክብር አጉልቶ ያሳያል። የሰውን ልጅ ክብር መርህ በመቀበል፣ የካቶሊክ ማህበራዊ አስተምህሮ የእያንዳንዱን ግለሰብ ውስጣዊ እሴት እንድንገነዘብ እና እንድንጠብቅ ጥሪ ያቀርብልናል፣ ተግባሮቻችን ፍትሃዊ እና ሩህሩህ ማህበረሰብን ለማሳደግ የሚችል መሆን እንዳለበት በአጽንኦት ይናገራል። ስለዚህ ወገኖቼ ከፈጣሪ በታች ከምንም በላይ ለሰው ልጅ ክብር ስጡ። የሰው ልጅ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ክቡር ፍጡር ነውና።

ይቀጥላል

**"እንግዲህ አግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምሃለን" (2ቆሮ. 5፡17)**

LINK

You are most welcome to
Subscribe and
Advertise on LINK

No. 270 October 2024 P. O. Box 2454 Tel. (0111) 55 03 00 Addis Ababa

# The 16th Catholic Church Synod of Holy Bishops was held at the Holy See




The 16th Catholic Church Synod of Holy Bishops was held at the Holy See from September 22 to October 17, 2017. Pope Francis officially opened the second phase of the regular meeting of the Holy Synod with a prayer at St. Peter's Square.

During the opening, Pope Francis emphasized the need for the Church to be humble and synodal, guided by the Holy Spirit, to fulfill its mission of peace and forgiveness in the world. He reflected on the synodal journey that had taken place.

His Holiness reminded the conference participants that the Church has been fulfilling God's mission for the people since the time of the apostles. The Synod included a three-year consultation to gauge the views of Catholics worldwide. Pope Francis opened what is commonly referred to as the Episcopal Conference to some of the faithful, including about 60 women among the 368 voters.

In his address at the Mass that officially launched the conference, the Pope urged the Church to continue on the synodal path, emphasizing the importance of prayer and listening. He highlighted the necessity of listening to the people's voices and treating one another with humility and respect, as one would treat siblings.

On September 27, 2017, Pope Francis declared a day of fasting and prayer for world peace and human unity. On this day, prayers were offered for Catholics facing war, famine, and other dangers.

Representing the Catholic Church of Ethiopia at the Synod, His Beatitude Cardinal Abune Birhane Jesus and His Beatitude Abune Markos, the Bishop of Jimma Bonga Diocese, were present during the sessions held from September 22 to October 17, 2017.

The Synod concluded on Sunday, October 17, 2017, with a closing Mass presided over by Pope Francis in St. Peter's Basilica. His Holiness continued the synodal journey that began three years prior with meetings at the national, regional, and continental levels, culminating in 2016. After the Vatican meeting in October, the attendees expressed gratitude to God for completing their joint journey.

At the closing Mass, Pope Francis encouraged the faithful to emulate Bartholomew by "entrusting our blindness to the Lord" and to "become a missionary Church that walks with the Lord on the road of the world." The results of the synod will be communicated to the faithful, and the bishops have called on the entire People of God to walk together in the joy of Christ. Saint Paul VI established the Holy Bishops' Conference of the Catholic Church in 1965.

# Pope Francis canonizes 14 new saints

In a Mass in St. Peter’s Square on Oct. 20, the pope declared three 19th-century founders of religious orders and the 11 “Martyrs of Damascus” as saints to be venerated by the global Catholic Church, commending their lives of sacrifice, missionary zeal, and service to the Church.

“These new saints lived Jesus’ way: service,” Pope Francis said. “They made themselves servants of their brothers and sisters, creative in doing good, steadfast in difficulties, and generous to the end.”

The newly canonized include St. Giuseppe Allamano, a diocesan priest from Italy who founded the Consolata missionary orders, and St. Marie-Léonie Paradis, a Canadian nun from Montreal known for founding an order dedicated to the service of priests.

Also among the saints are St. Elena Guerra, hailed as an “apostle of the Holy Spirit,” and St. Manuel Ruiz López and his seven Franciscan companions, all martyred in Damascus in 1860 for refusing to renounce their Christian faith.

The final three canonized are siblings, Sts. Francis, Mooti, and Raphael Massabki, lay Maronite Catholics martyred in Syria along with the Franciscans.

Thousands of pilgrims prayed the Litany of the Saints together in St. Peter’s Square before Pope Francis declared the 14 as enrolled among the saints “for the honor of the Blessed Trinity, the exaltation of the Catholic faith, and the increase of the Christian life, by the authority of Our Lord Jesus Christ, and of the holy apostles Peter and Paul.”

“We confidently ask for their intercession so that we too can follow Christ, follow him in service, and become witnesses of hope for the world,” the pope said.

In his homily, Pope Francis highlighted how service embodied the lives of each of the new saints. “When we learn to serve,” he said, “our every gesture of attention and care, every expression of tenderness, every work of mercy becomes a reflection of God’s love. And so we continue Jesus’ work in the world.”

The Gospel for the Mass was chanted in Greek in addition to Latin in honor of the 11 Martyrs of Damascus.

Father Marwan Dadas, a Franciscan friar from Jerusalem, was among those who attended the canonization. He said the testimony of the martyrs from the Franciscan Custody of the Holy Land is especially meaningful to people who are suffering due to the ongoing war and violence in the region today.

“This is a good message to say that even though we have challenges — and it seems we have death continuously — we still have the light of God that is helping us and guiding us through these difficult periods,” Dadas told CNA.

“It’s an important message for me, and I hope it will be the message for all the people of the Holy Land, not only the Holy Land but for everybody. It is a message from God saying that he is always with us.”

*St. Giuseppe Allamano: a missionary heart*

*St. Marie-Léonie Paradis: ‘humble among the humble’*

*St. Elena Guerra: an ‘apostle of the Holy Spirit’*

*The Martyrs of Damascus: courageous witnesses of faith*

## Training provided on Safeguarding of Children and Vulnerable Adults

For the past four days, from October 24 to 27, 2024, training was provided to priests and seminarians on the care and protection of children and vulnerable adults at the St. Francis Institute of Philosophy and Theology in Addis Ababa.

The training was delivered by guests from the Amisea office in Nairobi (Kenya), namely the former Head of the Apostolic Service of Amisea, Reverend Father Emmanuel Chimombo, and his successor, Reverend Father Florence Rutaiwa, Mr. George Tuku, and Ms. Pauline Wanjiru. On behalf of the Ethiopian Catholic Bishops' Conference, Ms. Merhawit explained the nature of the care and protection of children and vulnerable adults and provided a general overview of the work that the Church has done and is doing in this area.

Priests, especially those preparing seminarians for the priesthood, received the training on the first two days, Thursday and Friday, while seminarians and sisters studying at the institute received the training on the weekend. Venerable Father Chimombo led the Sunday Mass and delivered the homily. In their sermon, they said that deciding to follow the Lord is an individual's choice and it is appropriate to be prepared to accept the consequences of that choice. The priests, seminarians, and sisters expressed their satisfaction with the training.

Reverend Abba Abera Makebo, Deputy Secretary General and General Representative for Apostolic Ministry of the Ethiopian Catholic Bishops' Conference, welcomed the guests and participants and opened the training with a prayer. Reverend Abba Abnet Abebe, Coordinator of Family, Faithful and Youth Apostolic Ministry, closed the program with a prayer.

# Visit from Ireland

On November 12, 2024, the Catholic Bishops’ Conference of Ethiopia warmly welcomed bishops from Ireland and a team from Trocaire. Cardinal Abune Berhaneyesus, along with General Secretary of the CBCE Abba Ketema Asfaw, CEO Ato Bekele Moges, and Pastoral Program Coordinator Abba Abera Makebo, held discussions with the visiting delegation.

The visitors included the Archbishop of Cashel and Emly, the Archbishop of Dublin, the Bishop of Killaloe Diocese, the Bishop of Kildare and Leighlin Diocese, the Bishop of Kilmore Diocese, and the Bishop of Ossory Diocese. They were accompanied by the CEO, the Head of Portfolio for Fragile and Conflict-Affected States, the Church Outreach Manager, and the Communication Director of Trocaire.

The discussions focused on the deep historical, religious, and cultural connections between Ethiopia and the Irish missionaries, as well as the pastoral and social structure of the Ethiopian Catholic Church. The group is visiting Tigray and meet with the Bishop of Adigrat to discuss ways to support the region amid its current challenges.

The participants explored potential collaborations, addressing pastoral and social aspects of the Ethiopian Catholic Church, as well as the socio-political situation and the pursuit of peace in the country.

**For God so loved the world, that he gave his only begotten Son, that whosoever believeth in him should not perish, but have everlasting life. John 3:16**

# Message of the Holy Father Francis for the XXXIX (39th) World Youth Day 2024

## Those who hope in the Lord will run and not be weary (cf. Is 40:31)

*Dear young people!*

Last year we set out on the path of hope towards the Great Jubilee by reflecting on Saint Paul's words, "Rejoice in hope" (Rom 12:12). In order to prepare ourselves for the Jubilee pilgrimage of 2025, this year we can take inspiration from the prophet Isaiah, who says: "Those who hope in the Lord… will run and not be weary" (Is 40:31). These words are taken from the so-called Book of Consolation (Is 40-55), which heralds the end of Israel's exile in Babylon and the beginning of a new age of hope and rebirth for God's people, who can return to their homeland thanks to a new "highway" that the Lord is presently opening up for his children (cf. Is 40:3).

Today, we too live in times marked by dramatic situations that generate despair and prevent us from looking to the future with serenity: the tragedy of war, social injustices, inequalities, hunger and the exploitation of human beings and the natural environment. Often the ones who pay the highest price are precisely young people. You sense the uncertainty of the future and are not sure about where your dreams will lead. In this way, you can be tempted to live without hope, as prisoners of boredom, depression and even be drawn to risk-taking and destructive behaviors (cf. Spes Non Confundit, 12). For this reason, dear young people, I would like the message of hope to come to you, as was the case with Israel in Babylon. Today too, the Lord is opening a highway before you, and he invites you to set out on it with joy and hope.

### 1. The pilgrimage of life and its challenges

The prophet Isaiah speaks of "walking without tiring". Let us reflect then on these two realities: walking and tiredness. Our life is a pilgrimage, a journey that pushes us beyond ourselves, a journey in search of happiness. The Christian life in particular is a pilgrimage towards God, our salvation and the fullness of every good thing. Our goals, achievements and successes along the way, if they remain only material, will, after an initial moment of satisfaction, still leave us hungry, longing for something greater. They cannot completely satisfy our soul, because we were created by One who is infinite; as a result, we have an innate desire for transcendence, a constant restless drive towards the fulfillment of higher aspirations, towards "even more". That is why, as I have often said to you, "looking at life from a balcony" is not enough for you young people.

Still, it is normal that, while we set out on our journeys with enthusiasm, sooner or later we will begin to feel tired. In some cases, anxiety and inner fatigue are brought on by social pressures, the need to attain certain levels of success in our studies, our work and our personal life. This produces certain despondency, as we live running from one thing to another in an empty "activism" that makes us fill our days with a thousand things and, in spite of this, feel that we never manage to do enough and never quite measure up. This tiredness is often accompanied by a certain ennui, the apathy and dissatisfaction that affects those who never set out, choose, decide, take risks, preferring to remain in their own comfort zone, closed in on themselves, seeing and judging the world from a distance, without ever "dirtying their hands" with problems, with other people, with life itself. This kind of tiredness is a kind of wet cement in which we stand; eventually it hardens, weighs us down, paralyzes us and prevents us from moving forward. I prefer the tiredness of those who are moving forward, not the ennui of those who stand still with no desire to move!

The solution to tiredness, oddly enough, is not to stand still and rest. It is to set out and become pilgrims of hope. This is my invitation to you: walk in hope! Hope overcomes all weariness, every crisis and every worry. It gives us a powerful incentive to press forward, for it is a gift received from God himself. The Lord fills our life with meaning, sheds light on our path and shows us its ultimate direction and goal. The Apostle Paul uses the image of an athlete in the stadium racing to receive the prize of victory (cf. 1 Cor 9:24). Those of you who have taken part in a sports competition – not just as spectators but as athletes – know how much inner strength it takes to reach the finish line. Hope is precisely a new kind of strength that God instills in us, enabling us to persevere in the race, to see beyond present difficulties and to press forward to the goal of communion with him and the fullness of eternal life. If a beautiful goal exists, if life has an ultimate meaning, if nothing of what I dream, plan and accomplish will ever be lost, then it is worth the effort to keep walking, exerting ourselves, overcoming obstacles and fatigue, because the ultimate prize is magnificent beyond measure!

### 2. Pilgrims in the desert

In the pilgrimage of life, there will inevitably be challenges to face. In earlier times, long pilgrimages involved coping with changing seasons and climates, crossing pleasant meadows and cool forests, but also snow-capped mountains and parched deserts. Even for those who are believers, the pilgrimage of life and the journey to our ultimate goal can prove tiring, as the journey through the desert to the Promised Land was for the people of Israel.

And for all of you! Those who have received the gift of faith know happy moments when we can feel God's presence and closeness, but other moments too, when we experience the desert. It can happen that our initial enthusiasm for school or work, or for following Christ – whether in marriage, the priesthood or consecrated life – can be followed by moments of crisis, that make life seem like a difficult trek in the desert. Those times of crisis, however, are not wasted or useless: they can become important times of growth. They are moments when hope is purified! In crises, many false "hopes", hopes too small for our heart, fade into significance; they are revealed for what they are and we find ourselves alone in facing the fundamental questions of life, with no illusions. And in those times, each of us can ask: what are the hopes on which I have based my life? Are they real hopes or simply mirages?

At those times, the Lord does not abandon us. Like a father, he draws near to us and constantly gives us the bread that renews our strength for the journey. Let us remember that to the people in the desert he gave manna (cf. Ex 16) and to the prophet Elijah, weary and discouraged, he twice offered bread and water, so that he could walk for "forty days and forty nights to Horeb, the mountain of God" (cf. 1 Kings 19:3-8). In those biblical stories, the faith of the Church has seen prefigured the precious gift of the Eucharist, the true manna, the true food for the journey, that God gives us to sustain us on our way. As Blessed Carlo Acutis said, the Eucharist is the highway to heaven. Carlo made the Eucharist his most important daily appointment! In this way, in union with the Lord, we can walk without tiring, for he is walking alongside us (cf. Mt 28:20). I encourage all of you to rediscover the great gift of the Eucharist!

In those inevitable moments of fatigue in our pilgrimage in this world, let us learn, then, to rest like Jesus and in Jesus. He told his disciples to rest after they returned from their mission (cf. Mk 6:31); he also recognizes your own need for bodily rest, time for recreation, for enjoying the company of friends, for sports and for sleep. Yet there is a deeper kind of rest, the repose of the soul, which many seek and few find, for it is to be found in Christ alone. Realize that all your inner weariness can find repose in the Lord, who says to you: "Come to me, all you that are weary and carrying heavy burdens and I will give you rest" (Mt 11:28). When the weariness of the journey weighs you down, come back to Jesus, learn to rest in him and abide with him, for "those who hope in the Lord... will run and not be weary" (Is 40:31).

### 3. From tourists to pilgrims

Dear young people, I am inviting you to set out on a journey, to discover life along the path of love, and to seek the face of God. My advice to you is this: do not set out as mere tourists, but as true pilgrims. Do not be like superficial sightseers, blind to the beauty around you, never discovering the meaning of the roads you take, interested only in a few fleeting moments to capture in a selfie. Tourists do this. Pilgrims, on the other hand, immerse themselves fully in the places they encounter, listen to the message they communicate, and make them a part of their quest for happiness and fulfillment. The Jubilee pilgrimage is meant to be the outward sign of an inward journey that all of us are called to make towards our final destination.

With these attitudes, let us all prepare for the Jubilee Year. I trust that many of you will be able to come to Rome on pilgrimage to pass through the Holy Doors. In any case, everyone will be able to make this pilgrimage in his or her local Church, by visiting its churches and shrines that preserve the faith and devotion of God's holy and faithful people. It is my hope that this Jubilee pilgrimage will become for each of us "a moment of genuine, personal encounter with the Lord Jesus, the 'Door' of our salvation'" (Spes Non Confundit, 1). I encourage you to approach this experience with three fundamental attitudes. First, thanksgivings, with hearts open to praise God for his many gifts, especially the gift of life. Then, a spirit of seeking, as an expression of our heart's unquenchable thirst to encounter the Lord. And finally, penance, which helps us to look within, to acknowledge the wrong paths and decisions we have at times taken and, in this way, to be converted to the Lord and to the light of his Gospel.

### 4. Pilgrims of hope for the mission

Allow me to leave you with one more evocative image to guide your journey. Those who visit Saint Peter's Basilica in Rome cross the great square surrounded by the colonnade built by the celebrated architect and sculptor Gian Lorenzo Bernini. The entire colonnade appears as two open arms, an image of the Church, our mother, who embraces all her children. In this coming Holy Year of Hope, I invite all of you to experience the embrace of our merciful God, to experience his pardon and the forgiveness of all our "interior debts", as in the biblical tradition of the jubilee years. In this way, embraced by God and born again in him, you too can become open arms to embrace your many friends and peers who need to feel, through your welcome, the love of God the Father. May each of you give even just "a smile, a warm gesture of friendship, a kind look, a ready ear, a good deed, in the knowledge that, in the Spirit of Jesus, these can become, for those who receive them, rich seeds of hope" (ibid., 18), and thus become tireless missionaries of joy.

As we press forward, let us lift our gaze, in faith, to the saints who have gone before us on the journey, who have reached the goal and now encourage us by their testimony: "I have fought the good fight, I have finished the race, I have kept the faith. From now on, there is reserved for me the crown of righteousness, which the Lord, the righteous judge, will give me on that day; and not only to me, but also to all those who have longed for his appearing" (2 Tim 4:7-8). The example of so many saints, men and women, impels and sustains us.

Courage! All of you have a special place in my heart. I entrust your journey to the Virgin Mary, so that, following her example, you may be able to look forward with patience and confidence to the fulfillments of all your hopes, even now, as you persevere in your journey as pilgrims of hope and of love.

Rome, Saint John Lateran, 29 August 2024, Memorial of the Martyrdom of Saint John the Baptist.

This page is sponsored by CRS

**"Jesus defined eternal life saying, "This is eternal life, that they may know you, the only true God, and Jesus Christ whom you have sent" John 17:3**

# Catholic social teaching

## *Social justice and moral theology*



Catholic social teaching is a wealth of wisdom for building a just society and living a life of holiness amidst the challenges of modern society. Based on the Bible and Church tradition, this teaching is built on key principles.

Its main purpose is to consider, see and pay attention to the lifestyle of human beings of this era and what God expects from human beings by emphasizing the theological and moral thinking behind social justice. While this social teaching is very important and has the potential to bring meaningful change on earth; it is not being seen as it should be in the church and other institutions under the auspices of the church, such as schools, health institutions and others. It is observed that several organizations in the globe extracted some ideas from the CST and insert it in their own objectives and they achieve their significant organizational objectives. Things rarely resonate with the owners of the issue and are rarely implemented within the church and institutions under the umbrella of the church. Therefore, the purpose of this short article is that if all the institutions under the umbrella of the Church make this teaching a part of their work and implement it, I believe that it is definitely possible to bring about a meaningful change in attitude and thinking that emanate broad perception, strong will and intuition. What I am trying to do here is not to generate new ideas, but to enhance this great teaching and remind us to work together to bring about a better change.

We will continue to look at the main principles of Catholic social teaching with detailed explanations and relevant biblical references.

### 1. Human life and dignity

This principle emphasizes the inherent dignity and sanctity of every human life from conception to natural death. Every human being is created in the image and likeness of God and deserves respect and protection.

Human dignity is a fundamental principle in Catholic social teaching, and it says that every human being is created in the image and likeness of God and has inherent worth and dignity. Genesis 1:26-27 This honor proves that it is an internal and inviolable honor, which means that one of the main things that are important to our human being is respect for each other, regardless of the circumstances and actions, when this natural entity is distorted, the whole heart of the human being be broken; his soul be sad and his flesh be sick. A humiliated person whose human dignity has been affected will be mentally damaged more than people who wander without food, shelter and clothing or who are displaced by natural or man-made disasters. The personality of a human person would be affected, as soon as her/his dignity affected.

• "And God created mankind in His image, and in the image of God He created them male and female." Genesis 1:27

• "I knew you before I formed you in the womb, I set you apart before you were born, and I appointed you as a prophet to the nations." Jeremiah 1:5

The king replied, "I tell you the truth, what you did to one of the least of these brothers and sisters of mine, you did to me." Matthew 25:40

In this principle, Catholic social teaching supports the idea that every person needs respect and protection and deserves the opportunity to fully develop these issues as a human being what she/he strives to expand. It calls for the recognition of the unique value of each individual and emphasizes that human life is sacred from conception to natural death. This inner dignity is the foundation of human rights and is a central issue for social justice. Wherever human dignity is affected/humiliated, talking about social justice is worthless.

**Importance of these principles:**

- ***As the foundation of human rights:*** Human dignity is the cornerstone of human rights, so it emphasizes that all human beings should have their basic needs fulfilled and live free from oppression and injustice.
- ***Promotes Social Justice:*** Recognizing the inherent worth of each person, this principle motivates efforts to combat poverty, inequality and discrimination. It requires the creation of social conditions that allow individuals to reach their full potential.
- ***It is an ethical framework:*** It is presented as an ethical framework for evaluating social, economic and political systems. Policies and actions are judged on the extent to which they uphold and promote the human dignity of every person. Without human dignity, any policy and action is meaningless. Any political, economic and social thought or doctrine that ignores the rights of human beings will remain a voiceless cry.
- ***It is the foundation of community and solidarity:*** Recognizing the dignity of each person fosters a sense of community and solidarity. It encourages us to see others as brothers and sisters, helping us to increase love and compassion.
- ***Guides Moral Decision Making:*** This principle helps us make ethical decisions by reminding us to treat others with respect and consider the impact of our actions on their well-being. Any one's decision, whether individual or group, should firstly violate human dignity.

### 2. A call to family, community and participation

Family is a basic social institution and participation in community life is very crucial. As a human being is a social being, it is his inevitable nature to live together.

• **Human beings are not only sacred but also social.** The family is a central social institution that must be supported and strengthened. People have the right and duty to participate in society.

• The Lord God said: "It is not good for man to be alone; what suits them, let us create an assistant for him." Genesis 2:18

• "As we have many members in one body, and the work of all the members is not the same, so too When we are many, we are one body in Christ, and members of each other we are." Romans 12:4-5

"And God blessed them, and said to them, "Be many, multiply, and fill the earth, subdue it; Rule the fish of the sea and the birds of the air and everything that moves on the earth." Genesis 1:28

This section establishes the inner dignity of each person created in God's image It highlights for human beings to respect each other. He was created from the responsibility of God so that we can love and take care of the earth and its whole, not to create enmity with each other. It was not for him to perish and destroy creature. Therefore, knowing this, let us give the respect and love that human beings deserve, and let us protect and take care of other creatures. .

"When I saw the heavens, the work of your fingers, the moon and the stars, which you have made; What is a person to think about? What is a human being that you visit him? You made him less than the angels. You crowned him with glory and praise. You appointed him over all the work of your hands. You put everything under his feet. Psalm 8:3-5

My brothers, don't be partial to the faith of our Lord Jesus Christ. If a man wearing a gold ring and wearing fine clothes enters your assembly, and a poor man wearing dirty clothes also enters, and you look at the one wearing fine clothes and say to him, "Sit here in a good place," and if you say to the poor man, "You stand over there, or sit under my footstool," are you not separated? Are you not judges who have evil intentions? Listen, my beloved brothers; Hasn't God chosen the poor of this world to inherit the kingdom that God has given to those who love him to become rich in faith?
James 2:1-5

This section condemns discrimination and demands that all individuals be treated equally, recognizing their inherent dignity. This teaching clearly shows us that it is absolutely forbidden to discriminate, benefit or harm a person based on his poverty, wealth, race, tribe, language, religion, political opinion, or any reason.

As many verses of the Bible show us that Jesus Christ came from heaven from his Father to restore the honor that mankind lost in the Garden of Eden due to Satan. Especially the actions he took in dealing with the poor and marginalized people and the teachings he taught highlight the thoughts of Christ.

These verses show Jesus' commitment to uplifting the poor, the marginalized, and the socially disadvantaged, thus affirming the inherent dignity of every human being.

"There is neither Jew nor Gentile, there is neither slave nor free, there is neither man nor woman; for you are all one in Christ Jesus." Galatians 3:28

This part of the Bible emphasizes the equal dignity of all people regardless of social and cultural differences. Embracing the principle of human dignity, Catholic social teaching calls us to recognize and protect the intrinsic worth of each individual, emphasizing that our actions must be capable of fostering a just and compassionate society. Therefore, brothers and sisters, give honor to human beings above all else under the Creator. For the human being is a noble being created in the image of God.

to be continued

This page is sponsored by CAFOD/SCIAF/TROCAIRE

LINK

# የጥሪ ማዕድ

## የሕክምና ተልዕኮ እህቶች ማኅበር
## Medical Mission Sisters

*Called to be a healing presence at the heart of a wounded world*

**“ብርሃናችሁ በዓለም ሁሉ ይብራ”** ማቴ. 5: 16

“let your light shine” Mt. 5 - 16



ማህበራችን እ.ኤ.አ በ1925 በሲስተር አና ደንግል (ዶር) Sister Anna Dengel (Dr.) በአሜሪካ ተመሠረተ

**የማህበራችን ዋነኛው ዓላማ -** የክርስቶስን የማዳን ሥራ አገልግሎት በሕክምናና በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ።

**መስፈርታችን -**

- በቅድሚያ ሕይወቷን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎትና ለድሆች መስጠት የምትፈልግ
- ለጸሎትና ለእግዚአብሔር ትልቅ ስፍራ ያላት
- በዓለም አቀፍ ማኅበር መኖርና ማገልገል የምትፈልግ
- የትምህርት ደረጃ 10+2 እና ከዚያም በላይ

ቦሌ ጌስት ሃውስ አካባቢ
ቤት ቁጥር - 68
አድራሻችን አዲስ አበባ / ቂርቆስ - ወርዳ 01

የስልክ ቁጥር
0911055968
0911400139
0911106561
0923241466

ፖ.ሣ. ቁጥር 2891

| | |
|---|---|
| አድራሻችን | ወልቂጤ ጉራጌ |
| ስልክ ቁጥር | 011 3 30 52 37 |
| | ሲስተር ንግሥት ብሩ |
| ፖ.ሣ. ቁጥር | 11 |

## በአዲስ አበባ ካቶሊክ ሃገረስብከት ሴቶች ዕድገት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማዕከል

(ካሀሴዕማ/ቴ/ሙ/ት/ስ) አ.አ.

**Catholic Archdiocese Women's Promotion Technical and Vocational Education & Training Center**

(CAWPC / TVET) A. A

**“Come and see us. You will be most welcome! WE ARE WAITING FOR YOU!”**

በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኙና የቀለም ትምህርታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች አቋርጠው የሙያ ስልጠና ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶች ለማገዝ በአነስተኛ ክፍያ የስልጠና አገልግሎት በማግኘት ለሥራ ብቁ የሚያደርጉና ለገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴ የሚያዘጋጁ የሙያ ስልጠናዎችን በመስጠት ላይ እንገኛለን።

**በአጫጭር ስልጠና**
**(Short training)**
በደረጃ አንድና በደረጃ ሁለት
Level (1) one and Level (2) two

**የሚሰጡ ስልጠናዎች**

1 ልብስ ቅድና ስፌት
2 ህትመትና ማቅለም
3 የተሻሻለ የሽመና ሥራ
4 ጥልፍ በእጅና በስፌት መኪና
5 ሹራብ በእጅና በማሽን
6 ምግብ ዝግጅትና መስተንግዶ

ሀ - ከ 3-6 ወራት አጭር ኮርስና
ለ - ለ 10 ወራት በመረጡት ሙያ ሰልጥነው እራስዎን ለሥራ ያዘጋጁ።

**በማዕከላችን የስልጠና አገልግሎቱ ቀጣይነት በጥራት የሚያመርታቸውን የዕደጥበብ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ በመግዛት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንጋብዛልን።**

**አድራሻችን**
አራዳ ክ/ከ ፒያሳ
ካቶሊክ ካቴደራል ት/ቤት
ቅጥር ግቢ ውስጥ

**ስልክ ቁጥር**
011 111 4786 / 011 157 5927

**E-mail**
cawpc@ethionet.et

**ስለ“ፍቅርና ሰላም ጋዜጣ” አስተያየት ካለዎት በስልክ ቁ. (0111) 55 03 00 በመደወል ለፍቅርና ሰላም ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ያካፍሉን!**



## የኮንሰላታ ማርያም ልዑካን እህቶች እና አባቶች ገዳም

“የኮንሰላታ የአጽናኝቷ ማርያም ልዑካን እህቶች እና አባቶች ገዳም ዓለም አቀፍ ተልዕኮ ያለው ሲሆን የገዳማችን ልዩ ምልክት እግዚአብሔር ኢየሱስን አጽናኝ አድርጎ ለዓለም እንደሰጠ እኛም ለዓለም ሁሉ የምሥራቹን ቃል ማብሰር ነው።”


**“.... ሕዝቤን አጽናኑ አጽናኑ” (ኢሳ. 40 :1)**

እኛ የአጽናኝቷ ማርያም ልዑካን እህቶች እና አባቶች በብፁዕ ዮሴፍ አላማኖ አማካኝነት ቶሪኖ በሚባል በጣሊያን ከተማ ገዳማችን ተመሰረተ።

የተጠራነውም በፍቅር እንድንኖርና በተጠራንበት የፍቅር ሕይወት የእግዚአብሔርን ቃል ላልሰሙት ለማብሰር ነው። ይህንንም የምናደርገው በሕብረት በመኖር፣ ዛሬ በምንገኝባቸው አገሮች፣ በአፍሪቃ፣ በእስያ፣ በአውሮፓ፣ በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ ከማህበረሰቡ ጋር በመኖር የተለያየ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንገኛለን።

**የገዳማችንን መንፈስ ለመከተልም ሆነ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር እና መፅናናት ላልደረሳቸው ለማድረስ ለምትሹ እህቶች/ ወንድሞች ሁሉ -** የገዳማችን መጠይቅ እንደሚከተለው ነው

1 በቅድሚያ ራሷን/ራሱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት መስጠት የምትፈልግ/ የሚፈልግ
2 የእግዚአብሔርን ቃል ላልደረሳቸው ማብሰርና የተልኮ ሕይወት ለመኖር ሙሉ ፍላጎት ያላት/ ያለው
3 10+3 ወይም ዲፕሎማ 12+3 Degree (ዲግሪ) ከዛም በላይ በማንኛውም ዘርፍ የትምህርት ማስረጃ ያላት/ ያለው
4 ለአባቶች 12ኛ ክፍል ይቀበላሉ



Our Lady of Consolata
Pray for Us

**“ታላቅነቴን በሕዝቦች መካከል ያውጃሉ” (ኢሳ. 66 :18)**

ስልክ
**0912-14-26-37**
**011-3-21-01-47 / 48**

የፖ.ሳ ቁጥር
**145069 / 22748**

አድራሻ
**ኮንሰላታ ሲስተሮች/ አባቶች አዲስ አበባ መካኒሳ ከመካነየሱስ ሴሚናሪ ፊት ለፊት**

**በላይ ተክሉ ብስኩት ቤት**
*Belay Teklu Pastry*
ለሰርግ
ለልደት
ለተለያዩ ግብዣዎች
የሚሆኑ ኬኮችን አዘጋጅቶ ይጠብቃችኋል
አድራሻችን
ልደታ መልሶ ማልማት ፓርክ ፊት ለፊት
አዲስ አበባ
የመ.ሣ.ቁ 1928
0911203273
0911208810
0913303412

**የካቶሊክ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ መጻሕፍት መደብር**
**Catholic Church Book Shop**
ፒያሳ - ካቴድራል ት/ቤት ገባ ብሎ በስተቀኝ
ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ
ስልክ: (0111) 55 03 00

**ወንጌልን በጋራ እንስበክ**
**ሌሎች ቢያነቡዋቸው ትምህርት ያገኙባቸዋል ብለው የሚያምኑባቸውን መጣጥፎች እና የወንጌል አስትምህሮዎች ይላኩልን**
ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ ስልክ - (0111) 55 03 00 ፋክስ (0111) 55 31 13 E-Mail - scpr@eccsdco.org